ምዕራፍ አምስት
መዳጅነት

" አመንዝሮች ሆይ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል" /ያዕቆ 4÷4/::

"ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ጽድቅ ከአመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣኦት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሣለሁ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። ስለዚህ ጌታ ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኩስንም አትንኩ ይላል። ሁሉንም የሚገዛ ጌታ እኔም እቀበላችኋለሁ። ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል። " /2ቆሮ 6÷14-18/ " ምስጉን ነው በከፋዎች ምክር ያልሄደ፣ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፣ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል። እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች፣ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፣ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፣ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል። ከፋዎች እንዲህ አይደሉም፣ ነገር ግን ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ ናቸው። ስለዚህ ከፋዎች በፍርድ ኃጢአተኞችም በፃድቃን ማህበር አይቆሙም። እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ያውቃልና የከፋዎች መንገድ ግን ትጠፋለች :: " /መዝ 1÷1-6/

መዳጅነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጎላ አይደለም

የእግዚአብሔርን ልጆች በተመለከተ መፅሐፍ ቅዱስ ስለወዳጅነት የሚለው ጥቂት ነው። እርግጥ ወዳጅነት የሚለው ቃል በብዙ ሥፍራ ተጠቅሶ ይገኛል። በዘፍጥረት፣ በምሣሌ፣ በማቴዎስና በሉቃስ መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል። ብዙውን ጊዜ የሚያመለክተው ከክርስቶስ ውጭ የሆኑ ሰዎችን ሲሆን በጌታ ላሉት ግን የሚያገለግለው አልፎ አልፎ ነው። በትክክል አስታውሼ ከሆነ ወዳጅ የሚለው ቃል ሐዋርያው ጳውሎስን

በተመለከተ ሁለት ጊዜ በሐዋርያት ሥራ ተጠቅመውበታል። አንድ ጊዜ በኤፌሶን በነበረ ጊዜ "ከእስያም አለቆች ወዳጆቹ የሆኑት አንዳንዶች ደግሞ ወደ እርሱ ልከው ወደ ጨዋታ ስፍራ ራሱን እንዳይሠጥ ለመኑት "/ሐዋ 19÷31/ ሌላው ደግሞ ወደ ሮሜ ሲሄድ " ... ዩልዮስ ፀጳውሎስ ቸርነት አድርጎ ... ወደ ወዳጆቹ እንዲሄድ ፈቀደለት።" /ሐዋ 27÷3/

በዚህ በአዲስ ኪዳን ሐዋርያው ዮሐንስም "ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል። ወዳጆችን በየስማቸው እየጠራህ ሰላምታ አቅርብልኝ / 3ዮሐ 15/። በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ክርስቲያን ወዳጆች የሚያመለክተው በጣም ጥቂት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም በዚህ ጉዳይ ላይ አያተኩርም።

እንደዚህ ዓይነቱ ግንኙነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምንድን ነው ጉልህ ስፍራ ያልተሰጠው ? ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ሌላ የሚያጎላው ግንኙነት ስላለ ነው። ይህም እህቶችና ወንድሞች የሚለው ነው። በጌታ ወንድሞችና እህቶች መሆን መሠረታዊና ቅድሚያ የሚሠጠው ጠቃሚ ነገር ነው። መጠንከር የሚያስፈልገውም ይህ እንጅ የወዳጅነት ጉዳይ አይደለም።

የወዳጅነት ትርጉም

1. <u>በፍቅር የተመሠረተ ነው</u>

በአማኞች መካከል ከሚኖረው ግንኙነት አንፃር ወደጅ መሆን ማለት ምንማለት ነው? ወዳጅነት በሽማግሌ፣ በወጣቶች፣ በባልና በሚስት፣ በአባትና በልጅ፣ በወንድምና በወንድም ፣ በእህትና በእህት መካከል ሊኖር ይችላል ። ወዳጅ መሆን ማለት ማፍቀር መቻልና እርስ በእርስ ወይም አንዱ ከሌላው ጋር ሕብረት ማድረግ መቻል ማለት ነው። ከተለመደው ግንኙነትም ያለፈ ነው።

የብዙ ሰዎች የግንኙነት መሠረት ጋብቻ ወይም የሰጋ ዝምድና ነው። ነገር ግን ወዳጅነት እነዚህን ሁሉ ወደ ጎን ትቶ ስለ ፍቅር ብቻ የሚናገር ነው። ወዳጅነት ከባልና ከሚስት፣ ከአባትና ከልጅ፣ ከእናትና ከልጅ፣ ከተማሪና ከአስተማሪ ግንኙነት ውስጥ የሚጨመር አንድ ታላቅ ነገር ነው። እንዲሁም አንድ ዓይነት ማህበራዊ አቋም፣ አንድ አይነት እድሜና አንድ ዓይነት ዓላማ ያላቸው ሰዎች የወዳጅነት ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል።

2. <u>በዓለምም ጠቃሚ ነው</u>

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከማመናችን በፊት ማለትም ጌታን እንደግል አዳኛችን አድርገን ከመቀበላችን በፊት በጌታ የወንድምና የእህት ግንኙነት የሚባል አልነበረንም። ለዚህም ለማያምኑ የዓለም ሰዎች ወዳጅነት በጣም ጠቃሚ ነገር የሆነው።። ነገር ግን ለእኛ በዚያ መንገድና ሁኔታ አይቀጥልም። ለዚህም ነው በአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ወዳጅነት በጥቂቱ የተጠቀሰው።በእግዚአብሔር ልጆች መካከል ጠቀሚታው በጣም የቀነሰ ነው።

ሰው በቤተሰብ ግንኙነት ወይም በማህበራዊ ግንኙነት ብቻ ሙሉ በሙሉ እረካለሁ ብሎ አያስብም። ስለዚህ የውስጥ ናፍቆቱን ለማርካት ወዳጅ ይፈልጋል። ምክንያቱም ወዳጅነት የሚመሠረተው በስጋ ዝምድና ሣይሆን በፍቅር ስለሆነ ነው። ብዙውን ጊዜ የእኛ ግንኙነት የሚመጣው በትውልድ ምክንያት ነው። የወዳጅነት ግንኙነት ግን የሚገኘው በራስ ምርጫ ነው። ስለሆነም በጌታ ከማመናችን በፊት ወዳጅነት በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ነው። እያንዳንዱ ሰው ስምንት፣ አስር ወዘተ ወዳጆች እንዲኖሩት ይፈልጋል። በጣም ተግባቢ ሰዎች ደግሞ ከመቶ የበለጡ ወዳጆች ሊኖሩአቸው ይችላል። እንደዚያ ዓይነት ወዳጅነት በጥብቅ የተገናኘና በፍቅር የሚያግባባ ነው። ክርስቲያን ከመሆናችን በፊት ወዳጅነት በሕይወታችን ውስጥ ጉልህ ስፍራ አለው።

አንድ ሰው ወዳጅ ከሌለው ሰዎች አንድ ችግር ይኖርበታል ብለው ያስባሉ። ስለሆነም እንዲህ ዓይነቱ ሰው ጥቂት ወዳጆች ብቻ ይኖሩታል።

<u>በዓለም ያለ ወዳጅነት ይቋረጣል</u>

አንድ ሰው በጌታ ኢየሱስ እንዳመነ ወዲያውኑ ከቀድሞ ወዳጆቹ እንዲለይ በእግዚአብሔር ታዟል።

1. <u>የእግዚአብሔር ጠላት ነው</u>

"እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል ። "/ያዕ 4÷4/ እዚህ ላይ "የዓለም" የሚለው ቃል "የዓለምን ሰዎች" ወይም "የማያምኑትን "ማለት ነው። የዓለማውያን ወዳጆች የምንሆነው ዓለምን ስንወድ ነው። እንዲህ ብናደርግ ደግሞ ራሳችንን የእግዚአብሔር ጠላቶች እናደርጋለን "ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም" / 1ዮሐ 2÷15/።

አዳዲስ አማኞች ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ልትነግራቸውና ከሁሉ በፊት ሊያደርጉ የሚገባቸው ወዳጆቻቸውን ሙሉ በሙሉ መተው ነው። እኔ ብዙ ጊዜ አዳዲስ አማኞችን "አሁን በጌታ አምናችኋል። ስለዚህ ጓደኞቻችሁን ፍፁም መተው ያስፈልጋችኋል። ልብሶቻችሁንና ሌሎችን ነገሮች እንደምትለውጡ ጓደኞቻችሁንም ፍፁም ለውጧቸው" እላለሁ። ስለ ምን እንደምናገር አውቃለሁ። አዳዲስ አማኞች ጓደኞቻቸውን ካልተው የወደፊት መንፈሳዊ ሕይወታቸው ጥልቀት የሌለውና ደካማ ይሆናል። አንድ ሰው በጌታ እንዳመነ ወዲያውኑ ከቀድሞ ወዳጆቹ ራሱን ነፃ ማድረግ አለበት። የጌታ ፍቅር ሲገባና የእርሱ ሕይወት በእኛ ሲሆን የዓለም ወዳጅ መሆን የማይቻል እየሆነ ይመጣል።

ነገር ግን ልናስተውለው የሚገባ እርሱን ለማፍቀር የዓለም ጠላቶች ሁኑ አላለም። ሰዎችን መንገድ ላይ ስናገኛቸው እንኳ በሃዘኔታ ራሳችሁን ነቅንቃችሁ አለፉ አላለም። " እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል "የሚለው ቃል የዓለምን ሰዎች እንደ ጠላቶቻችሁ እዩአቸው በማለት አይመክረም። ይህ ማለት ግን የቀደመው ጥልቅ ወዳጅነትና የጠበቀ ግንኙነት ወደ ፊት ሊቀጥል አይችልም ለማለት ብቻ ነው። የቀድሞ ወዳጆችን አሁንም ልትወድ ትችላለህ፣ ነገር ግን ዓላማህ እነርሱን ለማዳን መሆን አለበት ። እንደ ጓደኛ ልትቀርባቸው ትችላለህ ነገር ግን ዓላማህ ወንጌልን እንዲሰሙ ለመጋበዝ ነው። ቆርኔሊዎስም ያደረገው ይህንኑ ነው። የጴጥሮስን መልዕክት እንዲሰሙ ሁለት ወገኖችን በቤቱ ጋበዘ። አንደኛው ወገን ዘመዶቹ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የቅርብ ወዳጆቹ ነበሩ። ስለዚህ አንተም ዘመዶችህንና የቅርብ ወዳጆችህን ወንጌል እንዲሰሙ አምጣቸው። ዓላማህ የቀደመውን ግንኙነታችሁን ለመጠበቅ ሳይሆን እነርሱን ወደ ጌታ ለማምጣት ነው። አንድ ሰው ጋር አንድ ጊዜ ከተዋወቅህና ከዚያ ሰው ጋር ያለህን እውቂያ ማቆም አትችልም። አንድ ሰው ወዳጅ ከሆነ አሁንም ወዳጅ ነው። እንግዲህ ለብዙ ዘመን ወዳጅ የሆንከውን ሰው ግንኙነቱን እንዴት ነው ልታቋርጥ የምትችለው? እዚህ ላይ እኛ በእውነት የምንለው ወደ ጌታ በመምጣት አንድ ጊዜ ለውጥን ስለተለማመድን የቀደመው ግንኙነት አይኖርም ማለታችን ነው። እርግጥ የቀደሙ ጓደኞቻችንን ስናያቸው አሁንም እናነጋግራቸዋለን። ችግር ሲገጥማቸውም እናወያያቸዋለን፣ ነገር ግን እኛ አዲስ ሕይወትን የተቀበልንና እነርሱ ደግሞ ያልተቀበሉ ስለሆነ ሊጣሰ የማይቻል የወሰን ግንብ በመካከላችን አለ።

በጉዞ ወይም በሩጫ ጊዜ ቀላል ሸክም የተሻለ ነው። በመንፈሳዊ ነገርም ከኃጢአት ጋር ያለንን ነገር ማቋረጥ ሸክሙን ያቀልልናል። ወዳጆችን መጨመር ሩጫችንን ሊያደናቅፈው ይችላል። እኔ ወዳጆቻቸው የተጫኑአቸውና ሸክም የሆኑባቸው ብዙ ወንድሞችና እህቶች አውቃለሁ።

እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር በፊታቸው ያስቀመጠውን ሩጫ እንደሚገባ ሊሮጡ አልቻሉም። የማያምኑ ሰዎች የተለየ የምግባር ደረጃ አላቸው። እነዚህ ሰዎች ጎትተው ባያወርዷችሁ እንኳ ወደ ላይ ግን ላያዘልሉአችሁ ይችላሉ።

2. <u>በማይመች አካሄድ አትጠመድ</u>

"ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ።"/2ቆሮ 6÷14/ ብዙ ሰዎች ይህን ጥቅስ ለጋብቻ ብቻ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። እኔ ግን ጋብቻንም እንደሚያጠቃልል አምናለሁ። አገልግሎቱ ግን ከዚያም በላይ ነው÷በሚያምኑና በማያምኑ ሰዎች መካከል ያለውን ወዳጅነትና ግንኙነት ሁሉ ያጠቃልላል። እዚህ ላይ አማኞችና የማያምኑ ሰዎች ፍፁም ሊስማሙ እንደማይችሉ ይነግረናል።

<u>በማይመች አካሄድ የመጠመድ ትርጉም</u>

"ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ " /2ቆሮ 6- 14/ የሚለውን ቃል ትርጉም ምን እንደሆነ ለማግኘት ከዚህ ጥቅስ ቀጥሎ ያሉትን አምስት ጥያቄዎች አንብብ "ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ጽድቅ ከአመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና ? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ሕብረት አለው? ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው ?ወይስ የማያምን ከሚያምን ጋር ምን ክፍል አለው? ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ከጣኦት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሣለሁ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናል።" (2ቆሮ 6÷14-16) እነዚህ አምስት ጥያቄዎች የሚያምኑና የማያምኑ ሰዎችን አንድ ቀንበር እንዲሸከሙ ማድረግ እንዴት እንደማይመች ይነግሩናል።

በማይመች አካሄድ መጠመድ መባረክ ሣይሆን እርግማንና ሐዘን ነው። እንግዲህ ከማያምን ሰው ጋር ያለን የጠበቀ ግንኙነት በማሕበራዊ ጉዳይም ይሁን በንግድ ዓለም በወዳጅነትም ይሁን በጋብቻ መጠበቅ እንደሌለብን ክርስቲያኖች እንደተረዱ ተስፋ አደርጋለሁ። አማኝ አንድ ያኗኗር ደረጃ አለው። አማኞች የእምነት ትምህርት አላቸው፣ የማያምኑት ደግሞ ባለማመን አስተምህሮ ይቀጥላሉ።አማኞች የእምነት አስተሣሠብ ይዘዋል። የማያምኑት ያለማመን አመለካከት አላቸው። እንግዲህ እነዚህን ባንድ ላይ ለማድረግና ለማምጣት ብትሞክር ውጤቱ በረከት ሣይሆን እርግማን ነው። አመለካከታቸውና አስተያየቶቹ የምግባር ደረጃቸውና ፍርዳቸው ከእኛ የተለየ ነው። እነዚህ ሁለቱ በሁለት አቅጣጫ ጀርባቸውን

ተሰጣጥተው የሚጓዙ ናቸው። እነዚህን ሁለቱን ባንድ ቀንበር ስር ማድረግ ቀንበሩን መስበር ነው። ያለበለዚያም የሚያምነው የማያምነውን ተከትሎ እንዲሄድ ማድረግ ነው።

አማኞች የማያምኑ ሰዎች ወዳጅ መሆን ኪሣራን ማምጣቱ የማይቀር መሆኑን እንዲረዱ እመኛለሁ። የማያምነውን መሳብ የምትችል መስሎህ እንዳታስብ። ይህን ሰው ካለበት ስቦ ለማውጣት ያንተን የጠበቀ ወዳጅነት አይጠይቅም። እኔ የቀድሞ ወዳጆቼን ያጣሁት ከእነርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረኝ ራሴን ሳላስገባ ነው። የዱሮ ግንኙነታችንን ሳንጠብቅ እነርሱን ማውጣት ይቻላል። ነገር ግን የዱሮ ወዳጅነታችሁ ከቀጠለ አንተ ራስህ በእነርሱ ተስበህ መውደቅህ የማይቀር ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ ሊ.ኤች. ስፖርጀን ጥሩ ምሳሌ ሰጥቷል። የሚከተለውን ታሪክ ማንበቡ የተሻለ ይመስለኛል። አንድ ወቅት አንዲት ወጣት ሴት ወደ ሰፐርጀን መጣችና ከአንድ ከማያምን ወጣት ሰው ጋር ወዳጅ ልትሆን ትችል እንደሆነ ጠየቀችው። ዓላማዋም ይህን ሰው ወደ ክርስቶስ ለማምጣትና ከእርሱም ጋር የጋብቻ ቃል ኪዳን ለማድረግ የወሰነች መሆኑን ነገረችው። ሰፐርጀንም ይህችን ወጣት ሴት ከአንድ ረጅም ጠረጴዛ ላይ እንድትወጣ ጠየቃት። ምንም ማድረግ ስለማትችል እሺ አለች። ሰፐርጀንም አስቀድሞ በእድሜ የጠና ሰው ስለሆነ እጁን እንድትጨብጠውና በተቻላት ጥረትና ኃይል ተጠቅማ ጠረጴዛው ላይ እንድታወጣው ነገራት። ሞከረች ግን አልቻለችም። ከዚያም ሰፐርጀን እርሷን ጎትቶ ማውረድ እንደሚችል ነገራት። ከዚያም አንዴ ብቻ ሲሰባት ወርዳ ቁጭ አለች። ሰፐርጀንም "ሰውን ጎትቶ ማውረድ ቀላል ነው ጎትቶ ማውጣት ግን የማይቻል ነው "አላት። የዚህች እህት ጥያቄ በዚሁ አልባት አገኘ።

ስለዚህ እናንተም የቀድሞ ወዳጆቻችሁን በጌታ ኢየሱስ ያመናችሁ መሆናችሁን ንገሩአቸው። ስታገኙአቸውም ወደ ጌታ አምጡአቸው። ወጣት በነበርኩ ጊዜ በትምህርት ቤት ብዙ ጓደኞች ነበሩኝ። በጌታ ካመንኩ በኋላ ወዳጆቼን ስጎበኝ መጽሐፍ ቅዱስ እይዝና ስለጌታ እነግራቸዋለሁ ያሣለፍኩትንም የውርደት ዘመኔን እንግራቸዋለሁ። ዱሮ ቁማር እንደምጫወትና ቲያትር ቤት እንደምሔድም እነግራቸዋለሁ። እነዚህን ነገሮች እንዳደርግ ዱሮ ወዳጆቼ ያሳምኑኝ ነበር። በጌታ ካመንኩ በኋላ ግን ከእነርሱ ጋር ስቀመጥ መጽሐፍ ቅዱሴን አወጣለሁ። በዚህም ድርጊቴ በሁሉም ዘንድ ወዲያውኑ እየታወቅሁ መጣሁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወዳጆቼ ወደ ቁማር ወይንም ወደ ቲያትር ሊሄዱ አይነግሩኝም። በቀደሙ ወዳጆቻችሁ ተጎትታችሁ ከምትወድቁ በእምነታችሁ ቅር ብታሰኟቸው ይሻላል። መጠነኛ ግንኙነት ቢኖር ችግር የለውም፣ ነገር ግን የጠበቀ ወዳጅነት አያስፈልግም።

ትሁትና የምትረዳቸው ሁን። ግንኙነትህ ግን ስር የሰደደ አይሁን። አንተ የጌታ ስለሆነልህ እነርሱንም ወደ ጌታ ማምጣት አለብህ።

በታማኝነት ጌታን ብታገለግልና ለእነዚህ ወዳጆችህ ጌታን ብታቀርብላቸው ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ ወደ ጌታ ይመለሳሉ ካልሆነም አንተን አይፈልጉህም። ከእነዚህ ሁለት አማራጮች ውጭ ሌላ መንገድ የለም።

<u>አምስቱ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች</u>

የመጀመሪው "ጻድቅ ከአመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለው ?" ይላል። አንድ ጊዜ በጌታ ካመንክ ፅድቅ ምን እንደሆነ ማወቅ አለብህ። አማኞች ፅድቅ የሆነውንና ያልሆነውን ለይቶ ማየትና ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። የቀደመውን የርኩሰት ሥራና ባሕርይ ማስወገድ አለባቸው። የሥነ ምግባር ሰዎች የሚባሉ ዓለማውያን አሁንም ጽድቅ ምን እንደሆነ አያውቁም። እንዲያውም ጽድቅንና አመፅን ያጋጩታል። አማኞች የሌሎችን ጥቅም ትንሽም ነገር እንኳን ብትሆን እንደማይነኩ ግልጽ ነው። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሌሎችን ጥቅም መውሰድ ይፈልጋሉ። በአንድ ወቅት የተቀበልካቸው ምግባሮች ዛሬ ፅድቅ እንዳልሆኑ ልትረዳ ትችላለህ። ስለዚህ እንደዚያ ባሉ ፅድቅ ባልሆነ ነገሮች ተካፍለህ ጽድቅን በአመፅ ለውጠህ ይሆናል። ነገር ግን ዝጽድቅ ጋር ምንም ዓይነት ተካፋይነት የለውም።

ሁለተኛው ደግሞ " ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ህብረት አለው?" የሚል ነው። አንተ ብርሃን የበራልህ ሰው ስለሆንህ አሁን በእውነተኛው ብርሃን ነገሮችን በትክክል ለማየት ትችላለህ። ነገር ግን የአንተ ዓለማውያን ወዳጆችህ በጨለማ ውስጥ ስላሉ የነገሮችን ትክክለኛ ባህርይ ለማየት አይችሉም። ከጌታ ጋር ብዙ መንገድ የተጓዙ የእግዚአብሔር ልጆች በጨለማና በድንግዝግዝ ከሚጓዙ ስጋዊ ክርስቲያኖች ጋር ህብረት ማድረግ አስቸጋሪ ሆኖ ያገኙታል። ታዲያ ያደጉ ክርስቲያኖች ምንም ብርሃን አይተው ከማያውቁት ጋር እንዴት ህብረት ማድረግ ይቻላቸዋል? አስተውል፣ በብርሃንና በጨለማ መካከል ምንም ዓይነት ሕብረት ሊኖር አይችልም። በጨለማ ያሉት አንተ ልታደርግ የማትችላቸውን ብዙ ነገሮች ማድረግ ይችላሉ። የእነሱ ፍልስፍናና ሥነ ምግባር፣ አመለካከትና የሕይወት ዓላማ ሁሉም ከአንተ ይለያሉ። አንተ በብርሃን ነህ እነርሱ ግን በጨለማ ናቸው። እንግዲህ የባህርይ ልዩነት ካለ እንዴት ህብረት ሊኖርህ ይችላል?!

ሦስተኛው ደግሞ "ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው?" የሚል ነው። እዚህ ላይ ቤልሆር የሚያመለክተው ሰይጣንን ነው።

ይህም ታል ከፋትንና ውርደትን ያመለክታል። ሰይጣን በትክክል የተዋረደና ክፋ ነው። እኛ የክርስቶስ ነን፣ የማያምኑት ግን የቤልሆር ልጆች ናቸው። እኛ በእግዚአብሔር ዓይን የከበርን ስንሆን እነርሱ ግን የተዋረዱ ናቸው ። እኛ በዋጋ የተገዛን ነን። የተገዛንበት ዋጋም የሚጠፋ ወርቅና ብር ሳይሆን በክበረው የእግዚአብሔር ልጅ ደም ነው። የእኛን የክርስትና ደረጃና ከብር የሚጥሱና የሚታረኑ የማናደርጋቸው ነገሮች አሉ። ስለሆነም ከቤልሆር ጋር መስማማት የለንም።

እነዚህ ሰዎች ግን የቤልሆር ናቸው። እኛ ልናደርግ የማንችላቸውን ብዙ ነገሮች ማድረግ ይችላሉ። የሌሎቹን ጥቅም ሊጋፉና በሌሎች ድካም የራሳቸውን ትርፍ መፈለግ ይችላሉ። እኛ ክርስቲያኖች ግን ክብርና ደረጃ አለን። ታዲያ እነዚህ ሁለቱ እንዴት ሊስማሙ ይችላሉ? እነዚህ ሁለቱ እንዴት አንድ አይነት ቀንበር ሊሸከሙ ይችላሉ? አንዱ ወደ አንድ አቅጣጫ ሲሰብ ሌላኛው ደግሞ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይጎትታል። በእንደዚህ ሁኔታ ውስጥ ሲጠመዱ ቀንበሩ ይሠበራል።

አራተኛው ደግሞ "የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?" የሚል ነው። እዚህ ላይ ደግሞ ሌላ ዓይነት ተቃርኖ አለ። አንተ የእምነት ሰው ነህ እነርሱ ግን የዕምነት ሰዎች አይደሉም። አንተ ታምናለህ እነርሱ ግን አያምኑም። አንተ እግዚአብሔርን በእምነት ታውቀዋለህ ትታመንበታለህም እነርሱ ግን እግዚአብሔርን አያውቁትም። እምነትም ስለሌላቸው ወደ ራሣቸው ይመለከታሉ። እናንተ ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነ ትመለከራላችሁ። እነርሱ ግን ሁሉ ነገር በእጃቸው እንደሆነ ይናገራሉ። እነዚህ ሁለቱ የማይገናኙ ሁኔታዎች ናቸው። ስለዚህ የሚያምን ከማያምን ምን ክፍል አለው? በእግዚአብሔር ማመን ለእናንተ እንደእስትንፋሣችሁ ነው። ለእነርሱ ግን እንደሚወዳቸው እንኳን ለማመን ከባድ ሆኖ ያገኙታል። እንዲያውም "ወግ አጥባቂ ናችሁ። ኋላቀር ናችሁ። ሞኞች ናችሁ" እያሉ ያጣጥሉአችኋል። ታዲያ እንዴት የማያምኑ ወዳጆች ሊኖሩን ይችላል። ከእነርሱ ጋር ወዳጅነታችንን ብንቀጥል ያለጥርጥር በፍጥነት ጎትተው ከራሳቸው ጋር ይጨምሩናል።

አምስተኛው ደግሞ "ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣኦት ጋር ምን መጋጠም አለው?" የሚል ነው። አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ማለት ምን ማለት እንደሆነና ጣኦት ማለት ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ እንመለከታለን። ይህ የሥጋን ቅድስና ያመለክታል ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም "እኛ የሕያው እግዚአብሔር ነን" ይላልና። በ1ኛቆሮንቶስ መልዕክት የሰው አካል የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆኑን እንመለከታለን። እዚህ ላይ ስጋዊ አካላቸው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆኑትን እናገኛለን። ሌሎች ደግሞ ጣኦት የሚያመልኩ አሉ።

ስለዚህ አንተ ከወዳጆችህ ጋር ስትሆን ብዙ ጊዜ የሚያደርጉት ሰውነትን የሚያረክሱ ነገሮች ስለሆነ ይህንን ቤተመቅደስ ታረክሳለህ። መጠጣት፣ ማጨስና የመሣሠሉትን ያደርጋሉ። ነገር ግን የአንተ አካል የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ስለሆነ ይህን ቤተ መቅደስ ማርከስ የለብህም። በቅድስና መጠበቅ እንጅ እኛ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ሆነን ከጣኦት ጋር ምን መጋጠም አለን? ምክንያቱም እነርሱ ከጣኦት ጋር ይገናኛሉና። እርግጥ ጣኦት የሚታይ ወይም የማይታይ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሰዎች የስጋን ቅድስና አይሹም፣ እኛ ግን እንሻለን። ስለ ስጋቸው ምንም ግድ እንደሌላቸው አላየንምን? እኛ ግን አካላችንን እናከብራለን፣ ንፁህ አድርገንም እንጠብቀዋለን።ስለዚህ እነዚህን ሁለት ዓይነት ሰዎች ማጋጠምና ማስማማት አይቻልም።

ስለዚህ ከማያምኑት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት አይኑርህ፥ካደረግህ ግን አንድ ውጤት ብቻ ይኖርሃል፣ ይህም ተጎትተህ ትወድቃለህ። ጥቂት የማያምኑ ወዳጆች ቢኖሩኝ አይጎዳኝም በማለት በጥንካሬህና በማይለወጥ አቋምህ ምንም አልሆን በማለት በማንነትህ አትመካ። አንድ ነገር ልንገራችሁ፣ ለብዙ ዓመታት ጌታን ስናምን የኖርን ቢሆንም እንኳ ከማያምኑ ወዳጆቻችን ጋር መገናኘትን አጥብቀን መፍራት ይገባናል። እንደዚህ ዓይነቱ ግንኙነት የእኛን መንፈሳዊ ሕይወት በቀላሉ ሊጎዳው ይችላል። የማያምኑትን ስትፈልግ ዓላማህ ወደ አምልኮ ቦታ ለመውሰድ አለዚያም ለመመስከር መሆን አለበት። ከዚያ ውጭ ያለ ግንኙነት ግን በጣም አደገኛ ነው። በመካከላቸው ከሆንህ ግን ደረጃህን በማሳነስ ራስህን ትደፋለህ። በእነርሱ መካከል የክርስቲያን ደረጃህን መጠበቅ ቀላል አይሆንልህም።

3. <u>የመጥፎ ንግግር ተፅዕኖ</u>

"አትሳቱ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።" /1ቆሮ 15÷33። "ክፉ ባልንጀርነት" ማለት ትክክል ያልሆነ ሀብረት ሲሆን ይህም እንጨት በትል እንደሚጠፋው እንዲሁ ዓይነት ባለንጀርነትም ያጠፋል።

<u>ጥፋትን ያመጣል</u>

"መልካም አመል" ለመልካም በሀርይ መግለጫ ነው። አግባብ የሌለው ግንኙነት ያንተን መልካም አካሄድ ያጠፋል። በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፊት ጥንቁቅ ልትሆን ትችላለህ። ነገር ግን በማያምኑ ወዳጆህ ሀብረት ምክንያት ሣቅና ጨዋታ ወይም ቀልድ ትጀምራለህ። ከቀንበሮችህ አንዱ ደግሞ የዋዘኛ ሳቅ አለመሣቅ ወይም አለመታለል ነው። ይህ ለክርስቲያን የማያምርና የማይስማማ ነው። ነገር ግን

በመካከላቸው ከተገኘህ ራስህን መቆጣጠር ደስ እንደሚያሰኛቸው ስለምታውቅ ወደ እነርሱ ትወግናለህ።

ክፋ ግንኙነት መልካሙን አመል ያጠፋል ማለት ይህ ነው። እነዚህ ሁለቱ የሚቃረኑ የሕይወት ልምምዶች ናቸው። ምክንያቱም አንደኛው ክፋ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መልካም ነው። ስለሆነም ክፋው መልካሙን ያጠፋዋል። ይህም በአማኞች ውስጥ ያለውን ከጌታ ያፇኑትን ሕይወት ያጠፋል። አማኞች ጥሩ ልምድ ሊኖራቸው ስለሚገባ በጌታ ፊት ይህን ልማድ ለማሣደግ ጊዜ ማጥፋት፣ ራሣቸውን መግዛትና መቆጣጠር አለባቸው። ቀስ በቀስ በመልካም ነገር ራሳቸውን ማስለመድ አለባቸው።

<u>መታደስ ጊዜ ይጠይቃል</u>

ሁል ጊዜ ከማያምኑ ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት ካለህ ኪሣራ ወይም ጥፋት ይገጥምሃል። ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ አንተንም ወደ ነበርህበት ቦታ ይመልስሃል። ለመታደስ ሦስት ወይም አራት አለዚያም ደግሞ አምስት ቀን ሊፈጅብህ ይችላል። ምክንቱም እነዚህ የማያምኑ ሰዎች የአንተን ጥሩውን አመልህንና ባህርይህን ተፅዕኖ ስለሚያሳድሩበትና ስለሚያበላሹት ነው።

4. <u>ከእነርሱ ጋር አትሂድ፣ አትቁም፣ አትቀመጥ</u>

መዝሙረኛው እንዲህ ይላል "ምስጉን ነው በክፋዎች ምክር ያልሄደ፣ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፣ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል ።" /መዝ 1÷1-2/

<u>በክፋዎች ምክር አትሂድ</u>

የማያምኑት ሰዎች የሚሰጡት ብዙ ምክር አላቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች ችግር ሲገጥማቸው የማያምኑ ሰዎችን ምክር መፈለግ በጣም የሚያሳዝን ነው። እኔ ልንገራችሁ የሚመክሯችሁ ሁሉ ማድረግ የማይገባችሁን ነው። እኔ ራሴ ብዙ የማያምኑ አማካሪዎች አጋጥመውኛል። እነዚህ ሰዎች ሳትጠይቋቸው ምክር እንደሚለግሱአችሁ አውቃለሁ። ነገር ግን እነዚህን ሰዎች ብትሰሙአቸው ሀሳባቸው በአንድ ነገር ላይ እንዳተኮረ አንድ ቀን ትረዳላችሁ። ይህም አንድ ሰው እንዴት እንደሚያተርፍ የሚያመለክት ነው። ይህ ነገር ትክክል ነው ወይንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለው አይጠይቁም። አንድ ፍላጎት ብቻ ነው ያላቸው። ያም የግል ትርፍ ነው። ታዲያ እኛ የራሳችንን ትርፍ ወይም ጥቅም ለመሻት የእነርሱን ምክር እንከተላለን? የእነርሱ ምክር ትርፍ

ወይም ጥቅም መሻት ብቻ ሳይሆን የሌሎንም ድካም ይፈለጋሉ። ታዲያ እንደዚህ ባለ ሁኔታ የሚያምን ከማያምን ጋር እንዴት ህብረት ሊያደርግ ይችላል?

የሚያምን ከማያምኑት ጋር ከተጣበቀ ከእነዚህ ብዙ መካሪዎቹ በስተኋላ አለመሄድ ይከብደዋል። ይህም ከክርስትና ደረጃህ ያወርድሃል። አምስት የማያምኑ ወዳጆች ቢኖሩህና ሁሉም በምክራቸው ቢስማሙ ያ ምክራቸው እንደሚጠቅምህ ቢስማሙ ይህን ምክራቸውን አለመከተል ላንተ አስቸጋሪ ይሆንብሃል።

በኃጢአተኞች መንገድ አትቁም

ልትሄድባቸው የማይገባ ብዙ ቦታዎች አሉ። ኃጢአተኞች የራሳቸው መንገድና ቦታ አላቸው። እንግዲህ ከማያምኑት ጋር ብትገናኝ ወደሚሄዱበት ቦታ ባትሄድ እንኳ በመንገዳቸው ላይ ግን መቆምህ የታመነ ነው። ይህም ወዳጅህን በር ለማዉጣትና ለመሰናበት እንደመሄድ ግለት ነው። ባትገባ እንኳ በመንገድ ላይ ግን ከእርሱ ጋር ነህ። እግዚአብሔር በከፉዎች ምክር እንድንሄድና በኃጢአተኞዎች መንገድ እንድንቆም አይፈልግም። ከኃጢአተኞች መንገድና ሥፍራ አውጥቶ ሊጠብቀን ይፈልጋል። እርሱ የጠራን ሙሉ በሙሉ ከእነርሱ እንድንለይ ነው።

በዋዘኞች ወንበር አትቀመጥ

አልፎ አልፎ አማኞች ባሉበት የማያምኑ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እያቃለሉ ሲያላግጡበት የማይታዩ በጣም ጥቂቶች ናቸው። በእኔ የመጀመሪያ የአራት ዓመት የክርስትና ሕይወቴ ብዙ የማያምኑ ሠዎች እኔ ባለሁበት ሊቀልዱ አጋጥሞኛል። የኢየሱስን ስም ይሳደባሉ፣ ታዲያ አንተ የኢየሱስ ስም እየተሰደበ በእነርሱ መካከል ትቀመጣለህ? እነርሱ ብቻቸውን ሲሆኑ የጌታን ስም አያነሱም ወይም የጌታን ስም አይሳደቡም፥ አንተ ስትመጣና ከእነርሱ ጋር ስትቀላቀል ግን አንተን ስለሚያዩ ኢየሱስን ያስባሉ፣ በዚህ ጊዜ በኢየሱስ ይስቃሉ። ክርስትናን ያጣጥሉታል። ታዲያ አንተ እንደዚያ ባለ ወንበር እንዴት መቀመጥ ትችላለህ? ስለዚህ በዋዘኞች ወንበር ላለመቀመጥ ከእነርሱ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት አይኑርህ።

አዲስ ዓይነት ወዳጅነት በቤተ ክርስቲያን

አማኞች ከዳኑ በኋላ ወዲያውኑ የወዳጅነት ጥያቄን ማሰብ፣ መሻትና ብሎም የቀድሞ ወዳጆቻቸውን መለወጥ አለባቸው። ለበፊት

ወዳጆቻቸውም ምን እንደሆነላቸው መንገር አለባቸው። እንዲህ ብታደርግ ጨርሰው እስኪተው ድረስ መጠነኛ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን በግልፅ የጠለቀና የጠበቀ ወዳጅነት መቀጠል የለበትም። ይልቁንም በቤተክርስቲያን እንዴት ወንድሞችና እህቶች እንደሚሆኑ መማር አለባቸው። በቀድሞ ወዳጆቻቸው ምትክ በቤተክርስቲያን ያሉ ወንድሞችን መተካት ይገባቸዋል።

መረን የወጣን መሆን የለብንም። የማያምኑትን አንጠላቸውም ነገር ግን አሁን ከእነርሱ ጋር በተለየ መልክ እንገናኛለን። ለእነርሱ ለመመስከርና ወደ ጌታ ለማምጣት እንማራለን። እነርሱን ልንጎበኛቸው ብንፈልግ እንኳ ማኅለፍ ያለብን ጊዜ ቢበዛ ለግማሽ ሰዓት ያህል ቢሆን ይመረጣል። ከእነርሱ ጋር ረጅም ጊዜ አትቀመጥ። ስለ አለም ነገሮችም አትነጋገር። በአዲሱ ደረጃህ ቁም። ወደ ጌታ ለማምጣት የተቻለህን ያህል ሞክር። ወደ ቤተክርስቲያንም ወስደህ ወንጌልን ስበክላቸው። ጥቂት ወንድሞችና እህቶች ወደ ቤታቸው ሄደው ወንጌልን እንዲነግሩዋቸው አድርግ። በጌታ የሆኑ ወንድሞችና እህቶችን ፈልግ። ከወንድማማችነት ውጭ የሆነ ወዳጅነት አትጠብቅ። ወዳጅነትህ በጌታ ከሆኑት ጋር ብቻ ይሁን።

አንድ ነገር ለማለት የምፈልገው ብዙ የማያምኑ ወዳጆች ያሉት አማኝ ያለ ጥርጥር ይወድቃል። ኃጢአትን ባያደርግ እንኳ ቢያንስ አለማዊ ይሆናል። ጌታን የሚያፈቅርና በታማኝነት የሚያገለግል ከሆነ ብዙ ዓለማዊ ወዳጆች ማፍራት ለክርስቲያን የማይቻል ነው። ያልነፃ አንደበት ጥፋት ነው። እንዲሁ ከንፈሮቻቸው በረከሱባቸው ህዝቦች መካከል መቀመጥም ስህተት ነው። ጥፋት የምንለው ኃጢአት ማድረግ ብቻ ሣይሆን በኃጢአተኞች መካከል መኖርም ጭምር ነው። በኃጢአት ከንፈራቸው በረከሰ ሕዝብ መካከል መኖር ከባድ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ኃጢአታችንን መናዘዝ ያስፈልገናል። ኃጢአት እንዳናደርግና ከኃጢአተኞች ጋር የጠበቀ ወዳጅነት መሻታችንን እግዚአብሔር ከእኛ እንዲያስወግደው ፀጋ እንዲሰጠን መለመን ይገባናል።

በመጀመሪያ ልንጠይቅ የሚገቡን ጥያቄዎች አሉ፡ሻነሌህም በቅድሚያ ሁኔታዬ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ነው? ከዚያም ከአማኞ ችስ ጋር ያለኝ ህብረት እንዴት ነው ? የሚሉ ይሆናልሉ ። እኛ በሌሎች የምንታወቀው በመጀመሪያ በእኛነታችንና ግንኙነታችንን ከማን ጋር እንደጠበቅን በሚሆነው መንገድ ነው ። አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ብርቱነቱን ጠብቆ ለመኖር ፍላጎት ካለው በህብረት ወይም በወዳጅ መስመር ቸልተኛ ሊሆን አይገባውም። ወዳጅነትን በተመለከተ ግዴለሽ ከሆነ ግን ወዲያውኑ ይሸነፋል። አማኞች በዚህ ጉዳይ ላይ መዘናጋት የለባቸውም። ከቀድሞ ወዳጆቻቸው ጋር በቁርጠኝነት ግንኙነታቸውን

መቀየርና መለየት ያስፈልጋቸዋል። በቤተክርስቲያን ህብረት ለማድረግ የዳኑትን መፈለግ አለባቸው። እንደዚያ ቢያደርጉ በጌታ እርስ በእርሣቸው ህብረት ሊኖራቸው ይችላል። ይህ በጌታ ያለ ህብረት የቀደመ ግንኙነታችንን ይተካል፣ ማትረፊያም ነው።

<u>ወዳጅነት በቤተክርስቲያን</u>

ወዳጅነት በጣም የተለየ ነገር እንደሆነ አያችሁ ? የወዳጅነት ግንኙነት ከምንገምተው ደረጃ በላይ ነው። ህጋዊ ወሰን የሚገድበው አይደለም። ከዚያም በላይ ነው። ይህ ዓይነቱ ህብረት የሥልጣንን ወይም የደረጃን ወሰን ወይም ገደብ ይሰብራል። ይህን ቀደም ሲል ተናግሬአለሁ፣ አባት አባት እንደሆነ ቢታወቅም፣ ልጅም ልጅ እንደሆነ ቢታወቅም አንዳንድ አባቶችና ልጆች ወዳጆች ወይም ጓደኛሞች ይሆናሉ። አንዳንድ ወላጆች ደግሞ ከልጆቻቸው ጋር ወዳጆች አይሆኑም። ግንኙነቸውም የወላጅና የልጅ ግንኙነት ብቻ ሆኖ ይቀራል። የወላጁና የልጁ ግንኙነት ገደብ አልፎ አይሄድም። ሕጋዊነቱን እንደጠበቀ ይቀራል። በብዙ ቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት ወዳጆች አይደሉም ግንኙነታቸው ከባልና ከሚስት አያልፍም። በብዙ ማህበረሰብ ብዙ አለቃና ሠራተኞች ወዳጆች አይሆኑም። የአለቃና የሠራተኛ ግንኙነት ህጋዊነቱን እንደጠበቀ ይቀራል። አልፎ አልፎ ግን ከዚያ ያለፈ ወዳጅነት ይገጥማል። ወዳጅ ማለት ከትክክለኛው ግንኙነት ያለፈ ጓደኛነት ማለት ነው።

<u>አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበረ</u>

ሰው ከሰው ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም ጋር ወዳጅ ይሆናል። አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር። አብርሃም እንደ ሰው ደረጃውን ቢጠብቅ፣ እግዚአብሔርም እንደ እግዚአብሔርነቱ ቢቀጥል ሁለቱ ወዳጆች ሊሆኑ አይችሉም። ወዳጆች ለመሆን ግን እግዚአብሔርም የራሱን ደረጃ መተው ነበረበት፣ አብርሃምም የራሱን ደረጃ መርሳት ነበረበት። ይህም አብርሃምና እግዚአብሔር ወዳጆች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

<u>ክርስቶስ የኃጢአተኞች ወዳጅ ነበረ</u>

ጌታ ኢየሱስ የኃጢአተኞች ወዳጅ ነው። በቦታው ብቻ ቢቆም ግን የኃጢአተኞች ወዳጅ መሆን አይችልም ነበር። ወዳጅ የሆነው ግን ያለበትን ከፍ ያለ ቦታ በመተው ነው። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ አዳኛችን እንጂ ወዳጃችን ለመሆን አይችልም ነበር። ክርስቶስ ወዳጅ ነበር ስንል ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ እንደሆነላችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ጌታና ኃጢአተኞች የማይታረቁ ናቸው። እርሱ ፈራጅ ነው፣ እኛ የዳን ነን።

ነገር ግን ጌታ የኃጢአተኞች ወዳጅ ሆነ። ይህን ሁሉ ተወው። ሰዎች የኃጢአተኞች ወዳጅ በማለት ይጠሩታል። ወዳጅ በመሆንም አዳኝ አድርገን እንድንቀበለው ሊመራን ችሏል።

የሐዋርያው ዮሐንስ ወዳጆች

እኔ አምናለሁ ዮሐንስ የእግዚአብሔር ልጅ ለጌታ ኢየሱስ ለብዙ ዘመናት ወንድም ሆኖ ከኖረና ከጌታም የሆነ ጥልቅ እውቀት ካለው በቤተክርስቲያን ላሉ አንዳንድ ሰዎች ወዳጅ ሊሆን ይችላል። ይህም በትክክል የአንድን ሰው ሕጋዊ ስልጣን ወይንም ደረጃ ያለፈ መሆኑን ያሳየናል። ይህንንም በሶስተኛው የሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክት ተገልጾ እናገኘዋለን።

ሶስተኛው የዮሐንስ መልዕክት የተፃፈው ሐዋርያው ጴጥሮስ በጣም አርጅቶ ሰማዕት ከሆነ ከሠላሳ ዓመታት በኋላ ይሆናል። ዮሐንስ መልዕክቱን ሲጽፍ ሽማግሌው ጴጥሮስ ወደ ጌታ ሄዷል። ሐዋርያው ጳውሎስም አልፏል። የቀሩትም አስሩ ሐዋርያት ከዓለም ተወስደዋል። ዮሐንስ ሲፅፍ እንደሐዋርያ ሳይሆን እንደ አንድ ሽማግሌ ሆኖ ነበር (ቁ.1)። የእርሱን ሶስተኛ መልዕክት በጣም እወደዋለሁ፣ ከሌሎች ከሁለቱ ፍፁም የተለየ ነው። በ1ኛ ዮሐንስ መልዕክቱ እንዲህ ብሏል "አባቶቼ "፣ "ወጣቶች ሆይ"፣ "ልጆች ሆይ" "ልጆቼ" በማለት ባለበት ደረጃ ሆኖ ይናገራቸዋል። ነገር ግን በሶስተኛው ዮሐንስ መልዕክት መጨረሻ አካባቢ በጣም በተለየ ቦታ ላይ ቆሟል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓለምን ትቶ ይሄዳል። በጣምም ሸምግሏል። እድሜውም ወደ ዘጠናዎች ነው። ስለ ጌታም ብዙ ያውቃል። ከጌታም ጋር ብዙ ሄዷል። ነገር ግን መልዕክቱን ሲፅፍ "ወንድሞቼ፣ እህቶቼ፣ ወጣቶች ሆይ፣ አባቶች" በማለት ፋንታ "ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል፣ ወዳጆችን በየስማቸው እየጠራህ ሰላምታ አቅርብልኝ።" /3ዮሐ15/ ይላቸዋል። የዚህን ጣዕም አገኘኸው? ወደዚህ መንፈስ መግባት ብትችል ትርጉሙን ትረዳዋለህ፣ አለበለዚያ ግን አይገባህም። ይህ ሰው በጣም የሸመገለ በመሆኑ ሁሉንም ወዳጆቹን አጥቷል። ጴጥሮስም ጳውሎስም ሞተዋል ። ነገር ግን አሁንም "ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል፣ ወዳጆችን በየስማቸው እየጠራህ ሰላምታ አቅርብልኝ።" ምን አይነት ፀጋ የበዛለት ሰው ነው! ወደ ዘጠናዎቹ ደርሷል፣ ለብዙ ዓመት ጌታን ተከትሏል፣ ብዙ ነገሮችንም ዳሷል እድሜም የጠገበ ሰው ነው። በስድሳና በሰባ ዓመቱ በነበረበት ሰዓት "ልጆቼ" እያለ ይጠራ ነበር፣ አሁን ግን እንደዚያ አላደረግም። ወደ ዘጠናዎቹ ሲገባ "ወዳጆቼ" እያለ ይጠራቸዋል፣ ያለበት ሕጋዊ ቦታ ተረስቷል፣ ካለበት ትልቅ ደረጃ ላይ ሆኖ ሌሎችን ከፍ ለማድረግ በወዳጅነት ይጠራቸዋል። ጌታ የኃጢአተኞች ወዳጅ እንዲሆን ነው።

እግዚአብሔርም አብርሃምን ወዳጅ እንዳደረገው ዮሐንስም በዚህ ቦታ ላይ ልጆችን፣ ወጣቶችንና አባቶችን እንደ ወዳጅ ያያቸዋል።

2. ወንድማማችነት

አንድ ቀን ወጣቶች በቤተክርስቲያን እንደዚያ ባለ ትልቅ ስፍራ ላይ ይደርሳሉ። ነገር ግን ዛሬ በወንድማማችነት ቦታ ወይም ሥፍራ ላይ መቆም አለባቸው። የወዳጅነት ጉዳይ በቤተክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚይዝ ነው። አንድ ቀን በጣም ስትበስል፣ ስትሸመግል ልጆችን ወዳጆች ልታደርግ ትችላለህ። በዚያን ጊዜ ግን በመንፈሣዊ ነገር ከእነርሱ በጣም የራቅህና የበሰልህ ነህ። ያን ጊዜ ወዳጆችህን ከፍ ማድረግ ትችላለህ። ያ ቀን እስኪመጣ ግን ቤተክርስቲያን የምታተኩረው በወዳጆች ላይ ሳይሆን በወንድሞችና በእህቶች ላይ ነው። ቤተክርስቲያን ከወዳጅነት ጉዳይ በስተቀር ብዙ ነገሮች ስታነሳ የሚያስገርም ነገር አይደለምን? ምክንያቱም ወዳጅነት በቤተክርስቲያን ውስጥ ደረጃና ሕግን የሚያልፍና ፍጹም በተለየ ቦታ ላይ የሚቆም ነው። ወዳጆች ለማድረግ ሌሎችን ከፍ ማድረግ ትልቅ ነገር ነው። ወዳጆች ብሎ በመጥራት ሌሎችን ከፍ ማድረግ የቻለ ታላቅ ሰው ነው። ነገር ግን ላላደጉ ወንድሞችና እህቶች አይሠራም። ወጣቶችና አዲስ የዳኑ ሰዎች በጌታ የወንድሞችንና የእህቶችን ግንኙነት መጠበቅን መለማመድ አለባቸው። ከቀድሞ ወዳጆቻቸው መለየ[illegible]ና ከቤተክርስቲያን ወንድሞና እህቶች ጋር ህብረት እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል።ይህም ጌታን በመከተል ከብዙ ችግሮች እንዲያመልጡ ይረዳቸዋል።

ምዕራፍ ሰድስት

ጋብቻ

የወሲብ ስሜት ኃጢአት አይደለም

ሰዎች የረሀብ ስሜት እንዳላቸው ሁሉ የወሲብ ስሜትም አላቸው። የወሲብ ስሜት እንደ ረሀብ ስሜት ሁሉ የስጋ ጥያቄ ነው። አንድን ሰው የረሀብ ስሜት ቢሰማው ይህ ስሜቱ ኃጢአት አይደለም። ነገር ግን ስሜቱን ለማርካት ምግብ ቢሰርቅ ስርቆት ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ ስለሆነ ኃጢአት ነው። የወሲብ ስሜትም ተፈጥሮአዊ እንጅ ከተፈጥሮ ውጭ ስላልሆነ እንደ ኃጢአት የሚቆጠር አይደለም። እንግዲህ አንድ ሰው በኃጢአት የሚወድቅ ይህን ተፈጥሯዊ ፍላጎቱን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ተጠቅሞ ለማርካት ሲሞክር ብቻ ነው።

የወሲብ ስሜት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሲሆን ጋብቻም በእግዚአብሔር የታዘዘና የተመሠረተ ነው። የተመሰረተውም ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት እንጅ ከወደቀ በኋላ አይደለም። ይህንንም በአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ ተገልፆ እናገኘዋለን። ከዚህም የምንረዳው ነገር ቢኖር የወሲብ ስሜት ኃጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱ በፊት የነበረ መሆኑን ነው። ስለዚህ አንድ ልናውቀው የሚገባ ጠቃሚ ነገር የ፞ወሲብ ስሜት ኃጢአት አለመሆኑን ነው። ምክንያቱም ጋብቻ በተመሠረተበት ወቅት ኃጢአት አልነበረምና!

በሰላሳ ዓመት የአገልግሎት ዘመኔ ብዙ ወጣት ወንድሞችና እህቶችን አግኝቻለሁ። በወሲብ ስሜት ምክንያት አንዳንዶች በቀላሉ የማይረበሹ ቢሆንም አብዛኞች ግን በከፍተኛ ሁኔታ ሲረበሹና ሕሊናቸውም አስፈላጊ ባልሆነ ነገር ሲከሳቸው አይቻለሁ። ለዚህም ምክንያቱ የእግዚአብሔርን ሃሳብ ስላላወቁና የቃሉም ምስጢር ስላልተገለፀላቸው ነው። የወሲብ ስሜት ስለተሰማቸው ብቻ ኃጢአት እንደሠሩ አድርገው ያስባሉ። ሌሎቹ ደግሞ ከዚያም አልፈው የወሲብ ስሜት ስላላቸው ብቻ እግዚአብሔር በእነርሱ ስለመሰራቱ ይጠራጠራሉ። ወሲብን እንደኃጢአት መመልከት የአሕዛብ አስተሳሰብ ነው ።

የእግዚአብሔር ቃል ስለጋብቻ ክቡርነት ሲናገር በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ይላል " መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ... ይሁን" /ዕብ 13:4/ ጋብቻ ክቡር ብቻ ሳይሆን ንፁህም ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የወሲብን ስሜት የሚያውቀው ተፈጥሮአዊ እንደሆነ ነው። በርካታ ለክርስትና ዕድገት ጠቃሚ መጽሐፍትን የጻፉት ዶክተር ኤፍቢ ሜየር ሲናገሩ ንፁህ ያልሆነ ኢዕምሮ ወሲብን እንደረከሰ ነገር

ይቆጥረዋል ብለዋል።ይህ ትክክለኛ አባባል ነው። አንድ ሰው ወሲብን ንፁህ እንዳልሆነ አድርጎ የሚያስብ ከሆነ አእምሮው ንፁህ አይደለም። እነዚህ ሰዎች ወሲብን የሚያስቡት የረከሰ እንደሆነ አድርገው ስለሆነ ለእነርሱ ርኩስ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው ጋብቻ ንፁህ ነው። በቅዱስ ጋብቻ ውስጥ የሚኖር ግንኙነት ቅዱስና ንፁሕ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በኋለኛው ዘመን ብዙ የስህተት ትምህርቶች እንደሚነሱ ፅፏል። ከስህተት ትምህርቶቹም መካከል " ... መጋባትን ይከለክላሉ" የሚለው ይገኝበታል (1ጢሞ 4÷3) ይህ የስህተት ትምህርት ከላይ ሲታይ ቅድስና ያለበት ይመስላል። አንድ ጂ.ኤች. ፔምበር የተባሉ ሰው በፅሁፋቸው ቅድስናን ለመከተል ሰዎች ከጋብቻ መከልከል እንዳለባቸው በግልፅ አስቀምጠዋል። ይህም ቅድስናን ያመጣል ብለው ያስባሉ። ነገር ግን በአንደኛ ጢሞቲዎስ ላይ እግዚአብሔር በግልጽ እንዳስቀመጠው ጋብቻን መከልከል ከመጨረሻው ዘመን የስህተት ትምህርቶች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ጋብቻን አልከለከለም።

ስለዚህ አማኞች በቃሉ እውቀት እንጅ በከንቱ ትምህርት ምክንያት ሕሊናቸው ሊከሣቸው አይገባም። ችግሩ የወሲብ ስሜት መኖሩ ሳይሆን ተግባራዊ ሲደረግ በኃጢአት መንገድ ሲሆን ይችላል። ከጋብቻ ውጭ ወሲብ ቢፈጸም ኃጢአት ነው።

ሶስቱ መሰረታዊ የጋብቻ ምክንያቶች

1. <u>በጋራ ለመረዳዳት</u>

ጋብቻ የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው። ለዚህም ነው እግዚአብሔር "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" /ዘፍ2:18/ በማለት የምትመቸውን ረዳት የፈጠረለት። እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠራትና ወደ አዳምም ያመጣት በስድስተኛው ቀን ሲሆን ይህም የጋብቻን ዓላማ ለመግለፅ ወይም ለማሳየት ነው። የሚመች ረዳት የሚለው ቃል ለመርዳት የሚመች ማለት ነው። ስለሆነም አዳምን መርዳት ከመቻሏ በፊት በቅድሚያ ልትመቸው ይገባል።

እግዚአብሔር ሲፈጥር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ይህም በመጀመሪያ ግማሹን አካል ቀጥሎም ደግሞ ሌላውን ግማሽ አካል በመፍጠር አንድ ሙሉ ሰው አደረጋቸው። ሁለቱ ግማሽ አካላት በአንድ ላይ ሲገናኙ ሙሉ ሰው ሆኑ። ከዚያም እግዚአብሔር "...እጅግ መልካም ነበረ" አለ። /ዘፍ 1:31/ ከሁሉ በፊት አንድ ሊታወቅ የሚገባው ነገር ቢኖር የጋብቻ ሀሳብ የመጣው ከእግዚአብሔር እንጅ ከሰው አለመሆኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ጋብቻ የተመሠረተው ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ሳይሆን ኃጢአት ከማድረጉ በፊት ነው። ሰው በተፈጠረበት

በመጀመሪያው ቀን ኃጢአትን አላደረገም። ጋብቻም የተፈጸመው በዚያው በመጀመሪያው ቀን ነው። እግዚአብሔር ሔዋንን ከፈጠረባት በዚያው ቀን ለአዳም ሰጣት። ስለዚህ ጋብቻ የተመሠረተው በትክክል በእግዚአብሔር እንደሆነ ግልፅ ነው።

በአራት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት ጋብቻ እንደተጀመረ እናያለን። በሌላ በኩል ደግሞ በዮሐንስ መንጌል ምዕራፍ ሁለት ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠበትን የቃና ዘገሊላ ሰርግ ተመዝግቦ እናገኛለን። እንግዲህ ይህ ድርጊት የሚያሳየን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋብቻን የፈቀደ ብቻ ሳይሆን ያፀደቀውም ጭምር መሆኑን ነው። በሰርጉ ላይ ተገኝቶ ሰርጉ እንዲሣካ አድርጓል። አስተውሉ ጋብቻን እግዚአብሔር መሠረተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አስረገጠው።

የእግዚአብሔር አላማ ለባል የምትረዳው ሚስት እንድትኖረው ነው። ለዚህም ነው ሚስት የምትመች ረዳት ተብላ የምትጠራው። እግዚአብሔር ባልና ሚስት በአንድ ላይ እንዲኖሩ ሕብረት እንዲያደርጉና እርስ በእርሳቸው እንዲረዳዱ ይፈልጋል። ይህ አንዱ የጋብቻ ምክንያት ነው።

2. <u>ዝሙትን ለመከላከል</u>

በብሉይ ኪዳን ኃጢአት ወደ ዓለም ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር ጋብቻን አስቀድሞ መስርቷል። ነገር ግን አሁን በአዲስ ኪዳን ዘመን ኃጢአት አስቀድሞ የመጣ ስለሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያው የቆሮንቶስ ሰዎች መልዕክት ምዕራፍ ሰባት ላይ ኃጢአት ወደ ዓለም በመግባቱ ምክንያት ጋብቻ የማይከለከል ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም እንደሆነ ይነግረናል።

ዝሙትን ለመከላከል እያንዳንዱ ወንድ ሚስት እንዲኖረው እያንዳንዱም ሴት ባል እንዲኖራት ሐዋርያው ጳውሎስ ይነግረናል። ሐዋርያው የወሲብ ስሜትን ኃጢአት ነው ብሎ አይኮንነውም። ይልቁንም ጋብቻ የዝሙትን ኃጢአት ሊከላከል እንደሚችል ይመክረናል።

ሐዋርያው "ምኞቱንም እንዲፈፅም ለስጋ አታስቡ" ይላል። /ሮሜ 13:14/ ይህ በጣም አስደናቂ ነገር ነው። አንድ ሰው ትዕቢተኛ ቢሆንና ኃጢአት ቢያደርግ ሐዋርያው ጳውሎስ "የትዕቢት ዝንባሌ ስላለህ ትዕቢት ብታሳይ ምንም አይደለም" ሊለው አይችልም። ይህ ምኞቱን እንዲፈጽም ለሥጋ ማሰብ ነው። እግዚአብሔር እንደዚያ ዓይነት ሀሳብን አይፈቅድም። አንድ ሰው ለመስረቅ ቢፈልግ ይህንን ሰው "መቸም ለመስረቅ ስለፈለግህ ሌላ ቦታ አትስረቅ እንጅ የወንድም እገሌ ንብረት

የሆነውን ይህንና ያን እፈትድልሃለሁ " አትለውም። በዚህ ፋንታ የምትነግረው «ኃጢአት ስለሆነ በየትኛውም ቦታ እንድትሰርቅ አልፈቅድልህም" የሚል ነው። ይህም በዚህ ጉዳይ ላይ ምኞቱን እንዲፈፅም ለስጋ አለመፍቀድ ነው። ትዕቢትም እንደዚሁ ኃጢአት ስለሆነ፣ ሊፈቀድለት አይገባም። ወሲብ ግን ኃጢአት ስላልሆነ በዚህ ጎራ የሚመደብ አይደለም። ተፈጥሯዊ የወሲብ ፍላጎቱን ለማርካት እያንዳንዱ ሰው የራሱ የትዳር ጓደኛ ሊኖረው እንደሚገባ ሁሉ እያንዳንዷም ሴት የራሷ የትዳር ጓደኛ ሊኖራት ይገባል በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ይመክረናል። ምክንያቱም የወሲብ ስሜት ኃጢአት አይደለምና ነው። ወሲብ ኃጢአት ቢሆን ኖሮ ሐዋርያው ጳውሎስ ምኞቱን እንዲፈፅም ለስጋ አታስቡ እንዳለ እናውቃለን፣ ወሲብን በተመለከተ ግን የትዳር ጓደኛ ይኑራችሁ ብሏል። እዚህ ላይ ልናስተውል የሚገባን ነገር እግዚአብሔር ጋብቻን የፈቀደው ስጋ ምኞቱን እንዲፈፅም በማሰብ አለመሆኑን ነው። ለዚህም ነው በእግዚአብሔር የተመሠረተ ቅዱስ ሥርዓት ነው በማለት የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው። ስለዚህ ጋብቻ እግዚአብሔር ይከብርበት ዘንድ የተመሠረተ ሥርዓት ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 7:9 ላይ ስለ ጋብቻ ሲናገር "ሚስት በገዛ ስጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፣ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጅ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ስልጣን የለውም ስልጣን ለሚስቱ ነው እንጅ" ይላል። በዚህ ጉዳይ ላይ መልእክቱ በጣም ግልፅ ነው። በቁጥር 5 ላይ " ለፀሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ " በማለት ይመክረናል። እንግዲህ ዝሙትን ለመከላከል ሲባል ባልና ሚስት መለያየት የለባቸውም። እግዚአብሔርም ጋብቻን በመፍቀድ ባልና ሚስት በአንድ ላይ እንዲሆኑ አዟል።

"ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና "/1ቆሮ 7:9/ ሐዋርያው ጳውሎስ እዚህ ላይ ጠንከር አድርጎ ይገልፀዋል። ለማግባት የሚያስገድድ ፍላጎት ያላቸውና በስሜት የሚቃጠሉ ሰዎች ማግባት አለባቸው። ስለእነርሱ ከፍተኛ ስሜት ያላቸውን ሰዎች የወሲብ ስሜታቸው ኃጢአት ነው ወይንም ስጋ ምኞቱን እንዲፈጽም አስባችኋል ብሎ አይገስፃቸውም። እንዲሁም ከፍተኛ ስሜት ያላቸውን ሰዎች በስሜት ከመቃጠል ይልቅ እንዲያገቡ ይመክራል። በዚህ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር ቃል ግልፅ ነው። የወሲብ ስሜት ኃጢአት አይደለም። ከፍተኛ የወሲብ ስሜት ቢሆን እንኳን ኃጢአት አይደለም። እንደነዚህ ላሉት ሰዎች በኃጢአት እንወድቃለን ብለው በመፍራት ከጋብቻ አይከልከሉ።

3. የሕይወትን ፀጋ አብሮ ለመውረስ

ጴጥሮስ ለባሎችና ለሚስቶች ሲናገር "... አብረው ደግሞ የሕይወትን ፀጋ እንደሚወርሱ... " ይላል /1ጴጥ3:7/። በሌላ አባባል አቂላና ጵርስቅላ፥ጴጥሮስና ባለቤቱ እንዲሁም ይሁዳና ባለቤቱ በአንድ ላይ እንዳገለገሉት ሁሉ ዛሬም እግዚአብሔር ባልና ሚስት ባንድ ላይ ሲ[illegible]ግሉት ይደሰታል።

የክርስቲያን ጋብቻ ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች እንዳሉት አማኞች ሁሉ ሊያውቁ ይገባል። አንደኛው በጋራ ለመረዳዳት ሁለተኛው ደግሞ ኃጢአትን ለመከላከል ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ፀጋን ለመከፋፈል ነው። ጋብቻ አንድን ክርስቲያን ብቻ የሚያቅፍ ሳይሆን ሁለት ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ፊት የሚጣበቁበትና አንድ የሚሆኑበት ስርዓት ነው። ጋብቻ አንድ ሰው ለብቻው ፀጋን የሚቀበልበት ስርዓት ሳይሆን በአንድ ላይ የሕይወትን ፀጋ የሚከፋፈሉበት ነው።

ድንግልና

መጽሐፍ ቅዱስ በእውነት አስደናቂ ነው። በአንድ በኩል ወሲብ ኃጢአት እንዳልሆነና ጋብቻም በእግዚአብሔር እንደ ተመሰረተ ኃጢአትንም ለመከላከል በእግዚአብሔር እንደታዘዘ ይነግረናል። ይህም ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች መልካም እንደሆነ ይነግረናል። በሌላ በኩል ደግሞ የወሲብ ፍላጎት የሌላቸው ሰዎች ድንግልናቸውን ጠብቀው ሊኖሩ እንደሚችሉ ይመክረናል።

1. የድንግልና ዓላማ

ድንግልና ከጋብቻ ይልቅ የበለጠ ቅዱስ አይደለም። ነገር ግን ድንግልና ለጌታ በሆኑ ነገሮች ላይ በሙሉ ኃይል ጠንቃቃ ለመሆን ስለሚያስችል ጠቀሜታ አለው።

ሐዋርያው ጳውሎስ መጋባት ሶስት ከባድ ችግሮች እንዳሉት ያሳየናል። ሀ) ጋብቻ መታሰር ነው። "በሚስት ታስረህ እንደሆንህ... "ይላል /1ቆሮ 7:27/። በጋብቻ ምክንያት ብዙ የሚያስፈልጉህ ነገሮች ይኖራሉ የሚያስፈልጉህም እነዚህ ነገሮች ጌታን በሚገባ እንዳታገለግል ያስሩሃል።

ለ) ጋብቻ መከራ ኢለው። "...እንዲህ በሚያደርጉ በስጋቸው ላይ መከራ ይሆንባቸዋል..." ይላል "/1ቆሮ 7:28/። እንደሚታወቀው ከጋብቻ በኋላ በስጋ ላይ የሚመጣ መከራ ይጨምራል። ስለዚህ ሀሳብህ ሳይከፋፈል ጌታን ማገልገል አትችልም።

ሐ) ያገቡ ስለ ዓለም ነገሮች ያስባሉ። "ነገር ግን ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል። ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፣ ልቡም ተከፍሎአል። ያልተጋባች ሴትና ድንግል በሥጋም በነፍስም እንዲቀደሱ የጌታን ነገር ያስባሉ። የተጋባች ግን ባልዋን እንዴት ደስ እንድታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች። " /ቆሮ 7:32 - 34/። እንደዚህ ዓይነቱ ሀሳብ ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ እንደተናገረው ስንዴ ፍሬውን እንዳይሰጥ እንክርዳድ በቀላሉ ሊያንቀው ይችላል። ስለጋብቻ ማሰብም ስንዴውን ሊያንቀውና ፍሬውን እንዳይሰጥ ያግደዋል። ስለሆነም ጋብቻ የራሱ ጫናዎችና ሸክሞች አሉበት። እነዚህም እስራት፣ መከራና ማሰብ ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረው ላገልጋዮች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ወንድሞችና እህቶች ጭምር ነው። ድንግልናውን ጠብቆ የሚኖር ሰው ከብዙ ችግሮች ወይም ጫናዎች ያመልጣል ።ሐዋርያው ስለ ድንግልና ባያዝም እንኳ ወደ ድንግልና ያዘነበለ ሀሳብ አለው። በዚህም እውነታዎችን በግልፅ አስቀምጧቸዋል። የወንድሞችና የእሕቶች መጋባት መልካም ስለሆነ የኃጢአትን አደጋ ሊያስወግድ ቢችልም ይታሠራሉ፣ በስጋቸውም ብዙ መከራ ይገጥማቸዋል፣ ስለ ሕይወታቸውም አብዝተው ያስባሉ።

2. ድንግልና ለማን ነው?

ሐዋርያው ጳውሎስ ድንግልናቸውን ጠብቀው መኖር ስለሚችሉ ሰዎች ነግሮናል።

ሀ. ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው

ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሰው ድንግልናውን ጠብቆ መኖር ይችላል። ድንግልና ስጦታ ነው። "ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የፀጋ ስጦታ አለው አንዱ እንዲህ ሁለተኛውም እንደዚያ . . .። " /1ቆሮ7÷71/ አንዳንዶች ማግባት ያስፈልጋቸዋል። ምክንያቱም የማግባት ፀጋ ተሰጥቷቸዋል፣ ያለዚህ ፀጋ ማንም ሊያገባ አይችልም። ጋብቻ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ሁሉ ድንግልናን ጠብቆ መኖርም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

ደናግል የወሲብ ስሜት የላቸውም ማለት ሳይሆን የሚያስገድድ የወሲብ ፍላጎት የላቸውም ለማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ሊኖራቸው ሌሎች ደግሞ የወሲብ ስሜት ብቻ ይኖራቸዋል። የሚያስገድዳቸው ወይም የሚገፋፋቸው ስሜት የሌላቸው ሰዎች ድንግልናቸውን ጠብቀው ሊኖሩ ይችላሉ።

ለ. <u>የፀና ልብ ያላቸው</u>

" ዳሩ ግን ማግባት ወደሚገባው ዕድሜ በደረሰ ጊዜ ስለ ድንግልናው ያፈረ ሰው ቢኖር የወደደውን ያድርግ ኃጢአት የለበትም ይጋቡ። ላይናወጥ በልቡ የፀና ግን ግድ የለበትም የወደደውን እንዲያደርግ ተፈቅዶለታል፣ ድንግልናውንም በልቡ ይጠብቅ ዘንድ ቢፀና መልካም አደረገ። " /1ቆሮ 7÷36-37/። በግሪኩ ድንግልና የሚለው ቃል ሴትን ልጅ አያመለክትም። አንድ ሰው ድንግልናውን በሚገባ መጠበቅ እንደሚይችል ካሰበ ሊያገባ ይችላል። ነገር ግን ድንግልናውን ጠብቆ የመኖር ፍላጎት ካለውና ፅኑ ልብና ቁርጥ ውሳኔ ካደረገ በድንግልናው መኖር ይችላል።

ሐ. <u>የአካባቢ ችግሮች የሌሉበት</u>

ድንግልናቸውን ጠብቀው ሊኖሩ የሚችሉ ሰዎች በመጀመሪያ የሚያስገድድ የወሲብ ፍላጎት የሌላቸው ነገር ግን የወሲብ ስሜት ሊኖራቸው የሚችሉ ናቸው። ሁለተኛ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለመኖር በጌታ ፊት በልባቸው የወሰኑ ናቸው። ሶስተኛ የአካባቢ ችግር የሌለባቸው። " ...ግድ የለበትም... "/1ቆሮ 7:37/ አንዳንድ ሰዎች የአካባቢ ችግሮች አሉባቸው። ስለሆነም ድንግልናቸውን በቀላሉ ጠብቀው ለመኖር ይቸገራሉ። ድንግልናቸውን ጠብቀው ለመኖር የማያስችሉ የቤተሰብ ግፊት ወይም ሌሎች ችግሮች ሊኖሩባቸው ይችላል። ስለዚህ በድንግልና ለመኖር የሚቻለው የአካባቢ ሁኔታም ተስማሚ ሆኖ ሲገኝ ነው። ግድ ያለባቸው ሰዎች ግን ድንግልናቸውን ጠብቀው ለመኖር አይችሉምና ሊያገቡ ይችላሉ።

3.<u>ድንግልና ከመንግስተ ሰማያትና ከመነጠቅ ጋር ያለው ግንኙነት</u>

ድንግልናውን መጠበቅ የሚችል ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብዙ ያተርፋል። በማቴ 19 ላይ የእግዚአብሔር ቃል ለድንግል ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት ቀላል ነው ይላል። ድንግልናና መንግስተ ሰማያት ልዩ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው በማቴ 19:12 ላይ ተገልጿል። "... ስለ

መንግስተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ ... " ግንኙነታቸውንም እንደሆነ መግለፅ አያስፈልገንም። ምክንያቱም ድንግልና ወደ መንግስቱ ለመግባት ጥቅም እንዳለው ከዚሁ መናገር እንችላለን። ጌታም አንዳንዶች ስለ መንግስተ ሰማያት ራሳቸውን እንደሰለቡ በግልጽ ነግሮናል። በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 14 ውስጥም እንደዚሁ ለእግዚአብሔርና ለበጉ የመጀመሪያ ፍሬ ስለሆኑት ስለ 144.000 ሰዎች የሚናገር ክፍል አለ። እነዚህ ሰዎች ድንግል ናቸው /ራዕ 14÷4/። በጉም ወደሚሄድበት ቦታ ሁሉ ይከተሉታል። ስለዚህ ድንግልና ከመነጠቅ ጋር ግንኙነት እንዳለው ይህ እውነት ያረጋግጥልናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ጋብቻ ቅዱስ ሲሆን አለማግባትም ቅዱስ ነው። ጋብቻ መልካም ቢሆንም ቅሉ አለማግባት ደግሞ የተሻለ ነው። አለማግባት ጌታን ለማገልገል ተጨማሪ ነጻነት ይሰጣል። ስለዚህ ይህ ጉዳይ መንድሞችና እህቶች በእግዚአብሔር ፊት ምርጫቸውን እንዲያስተካክሉ ግልጽ ሆኖ ሊቆቀመጥላቸው ይገባል።

<u>በጋብቻ ውስጥ ሌላኛው ወገን</u>

ጌታ ማንን ማግባት እንደምንችልና እንደማንችል ግልጽ በሆነ ሁኔታ አስቀምጦልናል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰዎች ጋብቻ በእነርሱ መካከል ብቻ እንዲወሰን በግልጽ ያመለክታል። በሌላ አባባል ጋብቻ የሚደረግ ከሆነ ሌላኛው ወገን ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል መሆን አለበት። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ከልል ውጭ ማግባት የለበትም።

1. <u>የብሉይ ኪዳን ትምህርት</u>

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ውጭ ማግባት እንደሌለብን የሚያረጋግጡ ብዙ ክፍሎች አሉ። ሙሴ በዘዳግም ምዕራፍ ሰባት ውስጥ ለእስራኤላውያን የሚከተለውን የማስጠንቀቂያ ቃል ተናግሯል " ከእነርሱም ጋር አትጋባ፤ ሴት ልጅህን ለወንድ ልጁ አትስጥ ሴት ልጁንም ለወንድ ልጅህ አትውሰድ። እንዳይከተለኝ ሌሎችንም አማልክት እንዲያመልክ ልጅህን ያስታልና የእግዚአብሔርን ቁጣ ያነድድባትኋል ፈጥኖም ያጠፋትኋል። " /ዘዳ 7÷3-4 /

እስራኤላውያን ከነአናውያንን እንዲያገቡ አልተፈቀደላቸውም ስለዚህ ወንድሞችና እህቶች በብሉይ ኪዳን ትምህርት መሠረት ለጋብቻ የሚታሰበው ሌላኛው ወገን የግድ ከእግዚአብሔር ህዝብ መካከል መሆን

አለበት። ከእምነታችሁ ውጭ የሆኑ የትዳር ጓደኞችን ለማግባት አትፈልጉ አታድርጉትም። ብታደርጉ ግን ያ ሰው ከጌታ መንገድ አስወጥቶ ሌሎችን አማልዕክት እንድትከተሉ ሊያደርጋችሁ ይችላል። ሚስት ባሏን ለመከተል እንዲሁም ባል ሚስቱን ለመከተልና ጣኦትን ለማምለክ በጣም ቀላል ነው። በመጋባታችሁ ምክንያት የሌላውን ጣኦታት ለማምለክ ቀላል ነው። ሙሴን ተክቶ የእስራኤልን ሕዝብ የመራውና ወደ ተስፋይቱ ምድር ያሻገራቸው ኢያሱም ይህንኑ በተመለከተ አስጠንቅቆቸዋል።

" እናንተ ግን ተመልሳችሁ በመካከላችሁ ወደ ቀሩት ወደ እነዚህ አሕዛብ ብትጠጉ ከእነርሱም ጋር ብትጋቡ እናንተም ወደ እነርሱ እነርሱም ወደ እናንተ ብትደራረሱ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚህች ከመልካሚቱ ምድር እስከትጠፉ ድረስ መውደቂያና ወጥመድ በጎናችሁም መግረፊያ በዓይናችሁም እሾህ ይሆኑባችኋል እንጂ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲያ እነዚህን አህዛብ ከፊታችሁ እንዳያሳድዳቸው ፈጽማችሁ እወቁ። " /ኢያሱ 23÷12-13 /። ኢያሱ የምድሪቱ ሰዎች መውደቂያና ወጥመድ እንዳይሆኑባቸው ለእስራኤላውያን አስጠንቅቆቸዋል። ምክንያቱም እንግዶች ሚስቶችና ባሎች የእግዚአብሔር ሰዎች ጨርሰው እስኪጠፉ ድረስ እሾህና መውደቂያ ስለሚሆኑ ነው።

<u>በምርኮም ዘመን በነበሩ ጊዜ</u>

ነህምያ የምርኮ ምድርን ለማየት ወደ ይሁዳ በተመለሰ ጊዜ ብዙ የእስራኤል ልጆች በተቀላቀለ ጋብቻ ምክንያት የአሁድን ቋንቋ ለመናገር እንኳ ካለመቻል ደረጃ ደርሰው ባገኛቸው ጊዜ ሰበሰበና ተናገራቸው። በመስማማትም ከእንግዶች ፍጹም እንዲለዩ አደረገ /ነህ 13÷23-27/ የአሕዛብ ሴቶችን ማግባት የሚያመጣው ችግር ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ ልጆች እናቶቻቸውን እንዲከተሉና እግዚአብሔርን ከአንተ ጋር ለማገልገል እንዲሰናከሉ ያደርጋል። አህዛብን ብታገባ በራስህ ዓይን እያየህ ልጆችህ ወደ ዓለም ይገባሉ። ይህም ከባድ ሀዘንን የሚፈጥር ነው።

እግዚአብሔር በሌላም ወቅት በነቢዩ ሚልክያስም በኩል እስራኤላውያንን ከዚህ ነገር እንዲታቀቡ ሲያስጠነቅቅና ሲገስጻቸው እንመለከታለን።

"እግዚአብሔር የወደደውን መቅደስ ይሁዳ አርክሶአልና የእንግዳውንም አምላክ ልጅ ሚስት አድርጎ አግብቶአልና ይሁዳ

አታልሎአል በእስራኤልና በኢየሩሳሌም ውስጥ ርኩሰት ተሰርቷል። " / ሚል 2÷11/

የአሕዛብን ሴቶች የእግዚአብሔር ህዝቦች ማግባት ማለት የእግዚአብሔርን መቅደስ ማርከስ ማለት ነው። ስለዚህ የክርስቲያን ጋብቻ በክርስቲያን ክልል መወሰን አለበት። ንጉሥ ሰሎሞንም ከነገሥታት ሁሉ ጠቢብ ነበር። ነገር ግን እንግዶች ሴቶችን በማግባቱ እንግዶች አማልክትን ለማምለክ ሚስቶቹን ተከትሎ በአህዛብ መንገድ ለመሄድ ከእግዚአብሔር መንገድ ወጣ። ስለዚህ ስለምታገቡት ሰው ተጠንቀቁ ። እግዚአብሔርን የማያውቅ ሰው የክርስቲያን የትዳር ጓደኛ እንዲሆን አይታጭም።

2. <u>የአዲስ ኪዳን ትምሕርት</u>

በአዲስ ኪዳንም ሐዋርያው ጳውሎስ ማንን ማግባት እንዳለብን በግልፅ አስቀምጦልናል።

<u>ስለ መበለቶች</u>

" ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታሰረች ናት ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነፃነት አላት።" /1 ቆሮ 7÷ 39/

<u>በማይመች አካሄድ አትጠመዱ</u>

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በፃፈው መልእክት ውስጥ ማንን ማግባት እንዳለብን ሲናገር " ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ... " ብሏል /2ቆሮ 6÷14/። ይህ ቃል በቀጥታ ጋብቻ ባይልም እንኳ ጋብቻንም የሚያጠቃልል ነው ። የሚያምኑና የማያምኑ ሰዎችን ወደ አንድ ግብ እንዲደርሱ በአንድ ላይ ማሰማራት ሁለት አብረው የማይሄዱ እንስሳት ለእርሻ በአንድ ቀንበር ውስጥ ማስገባትን ይመስላል። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር የሚከለክለው ነገር ነው ። እግዚአብሔር አማኝ ከማያምን ጋር አንድ ዓይነት ቀንበር እንዲሸከም አይፈቅድም። በብሉይ ኪዳንም ይህ የተወገዘ ነው። " በበሬና በአህያ ባንድነት አትረስ "/ ዘዳ 22÷10/። በሬ ረጋ ያለ ሲሆን አህያ ግን ችኩል ነው። አንዱ ወደ ሌላ መንገድ መሄድ ሲፈልግ ሌላው ደግሞ ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ ጉዞውን ያቀናል። አንዱ ወደ መንግስተ ሰማያት ሲገሰግስ ሌላኛው ደግሞ ወደ ሲኦል ይፈጥናል ። አንዱ ለመንፈሳዊ በረከት ቅድሚያ ሲሰጥ ሌላኛው ደግሞ ለምድራዊ ብልፅግና ትኩረት ይሰጣል። አንዱ ወደ አንድ አቅጣጫ ሲጎተት ሌላው ደግሞ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይስባል።

ይህ የማይቻል ሁኔታ ነው። እንዲህ አይነቱን ቀንበር ሊታገሱትና ሊቋቋሙት የማይቻል ነው። ከሁሉ በጣም ከባዱ ቀንበር ደግሞ ጋብቻ ነው። ሶስት ምሳሌዎችን ብናወዳድር:- በንግድ ከመወዳጀት፣ በጋራ ድርጅት ከመከፈትና በጋብቻ ከመጣመር ከባዱ ቀንበር ጋብቻ ነው። የቤተሰብን ኃላፊነት ባንድ ላይ መሸከም በእውነት አስቸጋሪ ነው። ስልዚህ የምታገቡት የትዳር ጓደኛ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሆነ አማኝ ሊሆን ይገባል። በግዴለሽነት የማያምንን ሰው ለጋብቻ አትምረጡ። ከማያምን ጋር ብትጠመዱ በታላቅ ችግር ውስጥ ወዲያውኑ ትወድቃላችሁ። አማኙ ወደ አንዱ መንገድ ይስባል ሌላኛው ደግሞ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይሸመጥጣል። አንዱ ሰማያዊ ስጠታዎችን ሲፈልግ ሌላኛው ግን ምድራዊ ሀብትን ይመለከታል። የእነዚህ የሁለቱ ልዩነት እጅግ የሰፋ ነው። በዚህ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ በጌታ የሆኑትን እንድናገባ ያዘናል።

<u>የማያምን ሰው አግብተን ከሆነ</u>

ይህ ችግር ነው። አንድ ወንድም ቀደም ሲል የማታምን ሴት ወይንም አንዲት እህት የማያምን ወንድ አገባች እንበል። እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ይህ ወንድም ወይንም ይህች እህት ምንድን ነው ማድረግ ያለባቸው? ይህ ቀደም ሲል ካየነው ችግር ይለያል። የመጀመሪያዎቹ ያላገቡና ገና የትዳር ጓደኛ የሚፈልጉ ናቸው። የዚህኛው ችግር ግን የማታምን ሚስት ወይም ባል ቀደም ሲል አግብተዋል። እንግዲህ ምንድን ነው መደረግ ያለበት?

1. <u>መለየት ከፈለገ ይለይ</u>

ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነን ከፍል ከ 1ቆሮ 7÷ 12-13,15 ላይ እናገኛለን።በቤተሰብ ውስጥ ችግር እንደሚፈጠር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌላት ውስጥ አስቀድሞ ተናግሯል። አንድ ሰው ብቻውን ሙሉ በሙሉ በጌታ ካመነ በቤት ውስጥ ችግርና ግጭት ይፈጠራል ። ሉቃስም የጌታን ቃል በወንጌሉ እንዲህ በማለት አስቀምጦታል " ከአሁን ጀምሮ በአንዲት ቤት አምስት ሰዎች ይኖራሉና። ሶስቱም በሁለቱ ላይ ሁለቱም በሶስቱ ላይ ተነስተው ይለያያሉ "/ሉቃ12÷52/። የዚህ ዓይነቱ የመለያየት ምክንያት ከቤተሰብ ውስጥ ጥቂቶቹ በጌታ በማመናቸው ነው። አንድ የማያምን ባል በሚስቱ እምነት ምክንያት ለመለየት ፈልጎ በጌታ እስካመንሽ ድረስ ከእንግዲህ በኋላ አልፈልግሽም ቢላት ይህች ሴት ምን ማድረግ አለባት? መልሱንም የጌታ ቃል በግልፅ "ይለይ " በማለት አስቀምጠውታል /1ቆሮ 7÷15/ ይህ ነገር ለማያምን ባል ብቻ ሳይሆን

ሚስትም ጭምር ነው። የማታምን ሴት ከሚያምን ባሏ ለመለየት ከፈለገች ትለይ።

እዚህ ላይ ግን አንድ ነገር ግልፅ ሊሆን ይገባል። የመለያየቱን ሀሳብ መጀመር ወይም መገፋፋት ያለበት የሚያምነው እንጂ የሚያምነው ወገን መሆን የለበትም። የማያምነው ሰው ከፈለገ መለየት ይችላል። የሚያምን ግን መለየት መፈለግ የለበትም። ቅር ሊሰኝ የሚገባው የማያምን እንጂ የሚያምን መሆን የለበትም። የማያምነው ወገን የትዳር ጓደኛው በጌታ በማመኑ ምክንያት የወደፊት ሁኔታውን የሚያጨልምበት መስሎ ከተሰማውና ቅር ከተሰኘ ይለይ። አብሮ ቢቆይ ግን ጌታ ያድነው ይሆናል። የማታምን ሚስት ወይም የማያምን ባል ከሚያምነው ወገን ጋር አብሮ ለመኖር ከተስማማ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚል ከሚስቱ ወይም ከባሏ ጋር ለመኖር ትችላለች። እግዚአብሔር የጠራን ለሰላም ነው። የማያምን በሚያምን ይቀደሳል ። በዚህም ምን አልባት የማታምን ሚስት ወይም የማያምን ባል ይድን ይሆናል ። መለያየት ካለ ግን ከማያምነው ወገን እንጅ ካማኑ መምጣት የለበትም። የማያምነው ወገን ለመለየት ካልጠየቀ ያችን ነፍስ ጌታ እንደሚያድናት እናምናለን። እንደዚህ ዓይነቱን ጌታ እንደሚያድን ቀላል አይመስልም ይሆናል። ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ እኛ በእምነት ፀንተን ልንቆም ይገባናል።

አንዳንድ ወንድሞችና እህቶች ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት ከሚያምኑ ሰዎች ጋር ጋብቻ ፈጽመው ይሆናል። ወደ ጌታ ሲመጡ በጋብቻቸው ችግር ቢፈጠር እነዚህ ሰዎች ምንድን ነው ማድረግ ያለባቸው?

1. <u>የማያምነው ጋብቻውን ማፍረስ ይችላል</u>

ጌታ የማያምኑትን እናገባ ዘንድ እንደማይፈልግ ግልፅ ነው። ነገር ግን አማኝ ሰው ቀደም ሲል አግብቶ ከሆነ ያ የተለየ ጉዳይ ነው። የማያምነው ወገን በፈቃደኝነት ጋብቻው እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላል። የማያምነው ወገን በእምነታችን ምክንያት ጋብቻውን ለማቋረጥ ጥያቄ ቢያቀርብ እኛን ሊሰማን አይገባም። መለየት ከፈለገ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይለይ።

2. <u>አማኙ በግዴለሽነት ትዳሩን ማፍረስ የለበትም</u>

የማያምነው ሰው እምነታችሁን ባይፈልግም ጋብቻችሁ እንዲቋረጥ ላይጠይቅ ይችላል። ምንም እንኳ የማያምነው ወገን በጌታ እንዳመናችሁ ቢያውቅም ትዳሩ እንዲቀጥል ሊፈልግ ይችላል። በዚህ ጊዜ ግን ማወቅ ያለባችሁ የጋብቻ ቃል ኪዳን ያደረጋችሁት በእግዚአብሔር ፊት መሆኑን ነው። ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ፊት የተፈፀመና

የተቀደሰ ስርዓት ስለሆነ ክርስቲያን ቃል ኪዳኑን በግዴለሽነት ማፍረስ የለበትም። ቃል ኪዳን የማፍረስ ጥያቄን በተመለከተ ቀድሞ ሊመጣ የሚገባው ከማያምነው ወገን መሆን አለበት። የማያምነው ወገን በትዳር መቀጠል የሚፈልግና ሀሳቡን የማይለውጥ ከሆነ ቃል ኪዳንህን የማከበር ግዴታ አለብህ። አንድ ክርስቲያን ቃሉን ከሰጠ ያ ቃል ተግባራዊ መሆን አለበት እንጂ መፍረስ የለበትም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃሉን ስለሚጠብቅ ነው። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ እኛም ከጌታ ደህንነት አግኝተን ደህንነት ልናጣ እንችል ነበር። ስለዚህ ጋብቻን ለማቋረጥ የማያምነውን ወገን ሀሳብ እንቀበላለን እንጂ እኛ አማኞች ለማፍረስ አንችልም። የማያምነው ወገን የማይስማማ ከሆነ ውሉ ተግባራዊ መሆን አለበት። " አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? ለባልንጀራው የሚመል የማይከዳም።" /መዝ 15/114/

ይህንን ጉዳይ በገባአን ሰዎች ታሪክ ውስጥ ልናየው እንችላለን /ኢያሱ 9/። የገባአን ሰዎች በተንኮል በእስራኤል ሕዝብ ላይ ለመነሣት አቀዱ። ለዚህም የደረቀና የሻገተ እንጀራ፥ያረጀና የተሰፋ ጫማ፣ አሮጌም ልብስ አድርገው በመምጣት አታለሏቸው። ከሩቅ አገርም እንደመጡና ኢያሱም በሰላም በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ቃል ኪዳን እንዲያደርጉ ለመኑት። በመጨረሻ ግን በትክክል ክትርብ አካባቢ የነበሩ ሰዎች እንደሆኑ ታወቀ። ይሁን እንጂ ቀደም ሲል ቃል ኪዳን ስለተደረገ እስራኤላውያን እነዚህን ሰዎች እንዲገድሉ አልተፈቀደላቸውም። በዚህ ፋንታ ግን ለጉባኤው እንጨት እንዲለቅሙና ውሃ እንዲቀዱ ተደረገ ይህም የሚያሳየው መፅሐፍ ቅዱስ ቃል ኪዳንን ስለመጠበቅ እንዴት ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው ነው። የማያምነው ወገን ቃል ኪዳን ለማፍረስ ከፈለገ ከቅጣት ነፃ ነኝ። ነገር ግን የማያምነው ወገን አብሮ ለመኖር በጉዳዩ ከገፋበት ትዳራችን በግድ መቀጠል አለበት። የገባአን ሰዎች ቃል ኪዳን በአንድ ወቅት በመጣሱ በእስራኤላውያን ላይ ከፍተኛ ቅጣትን አስከትሏል። ሳኦል በሰሜቱ ተገፋፍቶ የገባንን ሰዎች አረደ /2 ሳሙ 21/። በዚህ ምክንያት ሰማይ ጠልን መስጠት አቆመ። በምድሪቱም ላይ ረሃብ ሆነ ። ከዚህ በኋላ ዳዊት ከገባአን ሰዎች ጋር እርቅ ለማድረግ ምን እንዲያደርግላቸው ይፈልጉ ዘንድ ጠየቃቸው። የገባአንም ሰዎች ሰባቱ የሳኦል ልጆች በእንጨት ላይ እንዲሰቀሉላቸው ጠየቁ። ዳዊትም በዚህ ጥያቄ ተስማማ። ስለዚህ ቃል ኪዳንን በግዴለሽነት እንድናፈርስ እግዚአብሔር አይፈቅድልንም። ስለሆነም ማንኛውንም ቃል ኪዳናችንን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመጠበቅ ከዚህ መማር አለብን።

እንግዲህ እንዲህ ባለ የጋብቻ ጉዳይ የማያምነው ለመለየት ፈቃደኛ ካልሆነ የሚያምነው ወገን ለመለየት ጠርነት መግጠም የለበትም፣ ውላቸውና ቃል ኪዳናቸው መቀጠል አለበት።

3. ፍቶን በማሰብ ፋንታ የሚያምነው ወገን እምነቱን በማይነኩ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከማያምነው ወገን ጋር መስማማት ቢችል መልካም ነው

አማኝ ሊያደርግ የሚችለው ነገር ቢኖር እንደ እምነቱ በሆኑ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ መደራደር መቻል ነው። በመጀመሪያ አማኙ የማያምነውን ወገን አግኝቶ ጌታን በሚያገለግለው ነገር እንዲስማማ ማድረግ አለበት። በዚህ ላይ መደባበቅና መሸፋፈን አይገባም። ሰንደቅ አላማው ቀጥ ብሎ መውለብለብ አለበት። ክርስቲያን ጌታን ለማገልገል ማንም ጣልቃ ሳይገባ ነፃነት ሊሰጠው ይገባል። በሁለተኛ ደረጃ ለቤተሰቡ ልጆች በሚወለዱ ጊዜ በጌታ ትምህርት መሠረት ማደግ አለባቸው። ሰውዬው ወይንም ሴትዮዋ በጌታ ላያምኑ ይችላሉ። ነገር ግን ልጆች በጌታ ቃል እየተገሰጹ ማደግ አለባቸው። እነዚህ ሁለት ነገሮች እልባት ማግኘት አለባቸው። አለበለዚያ ግን አስቸጋሪ ሁኔታ ሊመጣ ይችላል። የአማኝ ከማያምን ሰው ጋር መኖር ያለ ጥርጥር ኪሣራ ነው። ነገር ግን በተቻለ መጠን ኪሣራውን መቀነስና ማሳነስ መቻል አለበት። ጌታን ለማገልገል ነፃነት እንዲኖረንና ልጆቻችን ወደ ጌታ እንዲመጡ መጠየቅ አለብን። ምክንያቱም ክርስቲያኖች ነንና። ስለሆነም እኛ ወደ ዓለም አንሄድም ነገር ግን ጌታን እንከተላለን። የማያምነው ወገን በዚህ ከተስማማ መልካም ነው። ካልተስማማ ግን በመብቱ ይጠቀም።

ከሚያምነው ወገን ሊመጣ የሚችል የፍች ጥያቄ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍች በግልፅ ያስቀምጣል መፋታት የሚፈቀደው በአንድ ሁኔታ ብቻ ነው። ዓለም ብዙ የተለያዩ ምክንቶችን በማቅረብ ፍችን ይፈቅዳል። መፅሐፍ ቅዱስ ግን በአንድ ነገር ብቻ ፍችን ይፈቅዳል። ይህም ዝሙት ነው። ፍች የሚፈቀደው በዝሙት ምክንያት ብቻ ነው ፤ ሌላ መንገድ የለም። የአዕምሮ መነካት ወይንም አካላዊ ድካም ለፍች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በግልፅ በማቴወስ 19 እና በሉቃ 16 እንዳስቀመጠው ፍች የሚፈቀድበት ምክንያት ዝሙት ብቻ ነው።

1. ጋብቻ የሚፈርሰው መቼ ነው?

በዝሙት ጊዜ ፍች ይፈቀዳል። በዝሙት ምክንያት ፍች የሚፈቀደው ለምንድን ነው ? የዚህ ምክንያቱ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለያየው ስለሚል ነው። በሌላ አባባል ባልና ሚስት በእግዚአብሔር ፊት አንድ አካል ናቸው። በዚህ መሠረት ፍች ማለት አንድነታቸውን ማ[illegible] ማለት ነው። ዝሙት አንድነታቸውን [illegible] ዝሙት የፈፀመው ሰው የባልና የሚስትን አንድነት አፍርሷል።

2. አንድነት ከፈረሰ በኋላ መፋታት ይፈቀዳል

ለምንድን ነው በዝሙት ጊዜ መፋታት የሚፈቀደው? ምክንያቱም ዝሙት ሲፈጸም አንድነታቸው ስለፈረሰ ነው። ባል ወይንም ሚስት የዝሙት ኃጢአት በፈፀሙ ጊዜ በባልና በሚስት መካከል ያለው አንድነት ይፈርሳል። ስለዚህ ሌላኛው ወገን ነፃ ነው። በመጀመሪያ አንድ አካል ነበሩ። ይህም አንድነታቸው መጠበቅ ነበረበት፣ ነገር ግን ይህ አንድነታቸው በአንደኛው ወገን ስለፈረሰ ሌላኛው ወገን ነፃ ነው። ስለዚህ ዝሙት የመፋታት ብቸኛ ምክንያት ነው ። ባል ዝሙት ቢፈፅም ሚስት ከፈለገች ልትተወው ትችላለች። እንደዚሁ ሁሉ ባልም ዝሙት የፈፀመች ሚስቱን ሊተው ይችላል። ቤተክርስቲያን ይህን መከልከል የለባትም። ነፃ የሆነው ወገን ሊፈታና ሌላ ሊያገባ ይችላል። መፋታት አንድነታችን ፈርሷል የሚል የአዋጅ ቃል ነው።

እንግዲህ ፍች ምንድን ነው? ፍች የአንድነት መፍረስ መግለጫ ነው። ይህ አንድነት ደግሞ የሚፈርሰው ዝሙት በተፈፀመበት ጊዜ እንጅ ፍች በተከናወነበት ወቅት አይደለም። ስለሆነም ፍች ከእንግዲህ አንድነት አይቀጥልም ብሎ የሚያውጅበት መንገድ ነው። ጋብቻ የአንድነትን መኖር እንደሚያበስር ሁሉ ፍች ደግሞ የአንድነቱን መሰያየት የሚያውጅ ነው። ስለዚህ ከዝሙት በኋላ መፋታት ይፈቀዳል። ፍች ያለዝሙት ምክንያት የማይቻል ነው። ማንኛውም የፍች ምክንያት ውጤቱ አመንዝራ ያደርጋል።

ጋብቻ አንድነት መሆኑን እንረዳ። ሁለት ሰዎች ሁለት እንደሆኑ አይቀጥሉም፣ ነገር ግን አንድ ስጋ ይሆናሉ። ዝሙት ይህን አንድነት ያፈርሳል። ፍችም የዚህን መፍረስ ያውጃል። ስለዚህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለያየው።

መበለቶች

መጽሐፍ ቅዱስ የትዳር ጓደኛቸው የሞተባቸውን ሰዎች እንደገና እንዲያገቡ ይፈቅዳል ።

ጋብቻ በሞት ያበቃል። በትንሣኤ የጋብቻ ግንኙነት አይቀጥልም። በትንሣኤ ሰዎች አያገቡም አይጋቡም። ጋብቻ የዚህ ዓለም ነገር ነው። መላዕክት አይጋቡም። ሰዎችም በትንሣኤ አይጋቡም። ጋብቻ በምድራዊ ኑሯችን ዘመን ብቻ የሚከናወን ስርዓት እንጂ የሚመጣው ዘመን አይደለም። ስለሆነም ጋብቻ በሞት ያበቃል። አንድ ሰው የትዳር ጓደኛው

ከሞተ በኋላ በሕይወት ያለው ወገን እንደገና ሊያገባ ይችላል ወይም ካለፈው ፍቅሩ የተነሣ ሳያገባ ለመኖር ይችላል።

የሮሜ ሰባትን ትምህርት እንመልከት እዚህ ላይ ሁሉም ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር የተጋቡ እንደሆኑ አድርጎ ያሳያል። ብክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አማካኝነት እንደገና አግብተናል። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ያሳየናል "ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና ባልዋ ቢሞት ግን ስለባል ከሆነ ሕግ ተፈትታለች። . . . ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም ። /ሮሜ 7፥ 2-3/። በሮሜ ሰባት ትምህርት መሰረት ለሕጉ ባንሞት ኖሮ የክርስቶስ መሆን አንችልም ነበር። ምክንያቱም ከሕግ ጋር ስለተጋባን አመንዝራ ያደርገናልና ነው። ነገር ግን በክርስቶስ አማካኝነት ለሕግ ሞተናል። ስለሆነም ዛሬ አመንዝራ ሳንሆን ክርስቶስን መምረጥ እንችላለን። ለሕግ ስለሞትንም አሁን ከክርስቶስ ጋር ተጣብቀናል። እንደዚሁም ሁሉ ዛሬ ቤተክርስቲያን መበለቶች እንደገና እንዳያገቡ የመከልከል ሀሳብ ሊኖራት አይገባም። የዚህ ዓይነት ሀሳብ ምንጩ ከአሕዛብ ነው ።

እርግጥ መበለቶች ሳያገቡ ቢኖሩ መልካም ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ድንግልናቸውን ጠብቀው እንደሚኖሩት ሁሉ "-ላላገቡና ለመበለቶች ግን እለሁ እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው "/1ቆሮ 7÷8/ በማለት ጽፏል። ለማገልገል እንደ ድንግል ብቾቾውን ቢኖሩ ፍፁም ትክክል ነው። ነገር ግን ትችትንና የሳለምን ኢስተሣሠብ በመፍራት እንደገና አለማግባት ትክክል አይደለም።

"እንግዲህ ቆነጃጅት ሊያጋቡ እፈቅዳለሁ "/1ጢሞ 5÷14/። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ለጢሞቴዎስ ፅፎለታል። እነዚህ ቆነጃጅት መበለቶች እንደገና እንደሚያገቡት ማግባት አለባቸው፣ ነገር ግን ጥያቄው እነዚህ ሰዎች በአካልና በአዕምሮ ፍላጎቱና ዝግጅቱ አላቸው ወይ? የሚል ነው። አንዳንዶች ብቾኝነት ይሰማቾዋል። ይህ የአእምሮ ችግር ነው። አንዳንዶች ቤተሰብ እንዲኖራቾው ይፈልጋሉ። ስለዚህ ባሏን ያጣች እህት ወይም ሚስቱን ያጣ ወንድም እንደገና ማግባታቾው ተገቢ ነው ። ክርስቲያኖች በዚህ ጉዳይ ላይ ሰውን ሊተቹ አይገባም።

የወሲብ ኃጢአት

1. ኃጢአት ምንድን ነው ?

ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ ወሲብ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር ወሲብ ትክክል እንደሆነ፣ የወሲብ ስሜትም ትክክል እንደሆነ፣ ወሲብ መፈፀምም ትክክል እንደሆነ ከቃሉ ያስገነዝበናል። የወሲብ ስሜት ትክክል ብቻ ሳይሆን ንፁህም ነው። ነገር ግን ይህ የሚሆነው በጋብቻ ግንኙነት ብቻ ሲወሰን ነው። በጋብቻ ከልል ውስጥ ከሆነ ትክክልም ንፁህም ነው። አዳዲስ አማኞች የወሲብ ስሜት ወይም የወሲብ ፍላጎት ኃጢአት እንዳልሆነ ሊያውቁ ይገባቸዋል። ይህ ንፁህ ነገር ነው። ይሁን እንጅ እግዚአብሔር በወሲብ ድርጊት ላይ አንድ ገደብ አስቀምጧል። ወሲብ ትክክል የሚሆነው በጋብቻ ውስጥ ግለትም በባልና በሚስት አንድነት ብቻ ነው።ግንኛውም ከጋብቻ ውጭ የሚኖር የወሲብ ድርጊት ኃጢአት ነው። ኃጢአት ምን እንደሆነ አያችሁ? ወሲብ ኃጢአት የሚሆነው ከጋብቻ ውጭ ሲፈጸም ብቻ ነው። ለምን? ምክንያቱም ወሲብ ከጋብቻ ውጭ የባልና የሚስትን አንድነት ያፈርሳል። ወሲብ ኃጢአት የሚሆነው ከጋብቻ ውጭ ተፈጽሞ አንድነትን ሊያፈርስ ነው እንጅ ወሲብ በራሱ ኃጢአት አይደለም። ይህን በእግዚአብሔር ፊት በግልፅ ልናየው ይገባል።

2. በፈቃድ መስማማት ኃጢአት ነው

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ አምስት እንዲህ ብሏል "ወደ ሴት ያየሁት የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል ።"/ማቴ 5÷28/። እዚህ ላይ "ያየ " የሚለው ቃል ፈቃድንም ይጨምራል ። "አየ" ሲል የወሲብ ፍላጎትን የሚጨምር ነው። ይህ ሴትን እንዲሁ መመልከት ሳይሆን ከልብ ፈቃድ ጨምሮ በወሲብ አቅጣጫ ማየትን የሚጠቁም ነው። እንዲሁ ሴትን መመልከት ምኞትን አይቀሰቅስም። ነገር ግን የወሲብ ፍላጎትን ጨምሮ ከልብ ማየት ከእርሷ በኋላ ምኞትን ያስከትላል ። ምኞት ከልብ ከማየት ቀጥሎ የሚመጣ ነገር ነው። ስለዚህ ይህ ማየት የሚለው በወሲብ አቅጣጫ ከልብ ማየትን ለመግለፅ ነው ። የዚህ አይነቱ አስተያየት በትክክል ፈቃድን የሚጨምር አደገኛ የሆነ እርምጃ ነው። አንድ ሰው ሴትን ሊያይ ይችላል። ይህ ችግር የለውም። ነገር ግን ከወሲብ አቅጣጫ ከልቡ ሲያያት ምኞቱ ይቀሰቀሳል። ይህ ምኞት ደግሞ በፈቃደ ሥጋ ተነድቶ በልብ ማመንዘር ነው። ማንኛውም ሰው ሴትን ያያል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን መቆጣጠር ስለሚያቅታቸው የምኞት ሀሳብ ይጀምራሉ። በመቀጠልም ይህንን ሰይጣን

የሚወረውርባቸውን ክፋ ሀሳብ ተቀብለው ያስተናግዳሉ። ይህ ኃጢአት ነው ።

በዚህ ዓይነት መንገድ ሴትን አይቶ የተመኘ በልቡ ዝሙትን ፈጽሟል። እዚህ ላይ የተጠቀሰው እንዲሁ ማየቱ አይደለም። አንድ ሰው ድንገት መንገድ ላይ ሴት ሊያይ ይችላል። ቢያያትም ሰይጣን ወደ አዕምሮው የሚወረውርበትን ክፋ ምኞት እስካላስተናገደ ድረስ ኃጢአት አላደረገም ። ነገር ግን ከልቡ ፈቃደኛ ሆኖ በወሲብ አቅጣጫ ካያት ያችን ሴት አየተመኛት ነው ። ከጋብቻ ውጭ ለወሲብ በሀሳብ ደረጃ በፈቃድ መስማማት በራሱ ኃጢአት ነው ። እንዲህ ዓይነት ሰው የጋብቻን አንድነት በፈቃዱ አስቀድሞ አፍርሷል። በሀሳቡም ሆነ በድርጊት ይህ አንድነትን የሚያፈርስ ኃጢአት ነው። ይህን አንድነት የሚያፈርስ ኃጢአት በሀሳብ ደረጃ ቢያከናውን እንኳ በድርጊት ከተፈፀመ ኃጢአት ጋር እኩል ነው ።

ምዕራፍ ሰባት
እጮኛን መምረጥ

"እግዚአብሔር አምላክም አለ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።" / ዘፍ 2÷18/

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ሁለት ግማሽ አካላት አድርጎ ፈጠራቸው። ስለዚህ ብቸኛ ሆነው እንዲኖሩ ፀጋው ከተሰጣቸው ጥቂት ሰዎች በስተቀር ሁሉም ሰው ማግባት አለበት። ብዙ የመፅሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች እንደሚያምኑበት አንድ የእግዚአብሔር ልጅ እጮኛ በሚመርጥበት ጊዜ ጥሪቱ ማተኮር ያለበት ሌላውን ግማሽ አካል ከመፈለጉ ላይ ነው። እጮኛ መምረጥ ማለት በቀላሉ አነጋገር ሁለቱ ግማሽ አካላት አንድ ሙሉ እንዲሆኑ እግዚአብሔር ለአንተ የፈጠረልህን ሌላውን ግማሽ መፈለግ ነው። በእድሜ የሸመገሉ ወንድሞችና እህቶች ወጣት የሆኑ አማኞችን እንዴት ሌላውን ግማሽ አካል እንደሚፈልጉ መምከርና ማስተማር አለባቸው። እንደዚህ ዓይነቱ ፍለጋ ዓላማው አንድ ሙሉ አካል ለማድረግ ነው። ግማሽ አካል ግማሽ እንደሆነ ከቀረ ውጤት አይኖረውም። ሌላውን ተጣማጅ አካል ማግኘት የቻሉ ሰዎች ሙሉ ይሆናሉ። ነገር ግን ሁለት ግማሾችን በዘፈቀደ አንድ ላይ ማድረግ ከፍተኛ ችግር ያመጣል፣ ያስከትላልም። እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው ሊለያየው እንደማይችል እናምናለን። ስለዚህ ወጣቶች እግዚአብሔር የሚያጣምራቸውን ግማሽ አካላት በትክክል መፈለግ ይገባቸዋል።

የወንድሞችና የእህቶች ጋብቻ በቤተ ክርስቲያን ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አለው። በጋብቻ ላይ ችግር ካለ ያ ችግር ወዲያውኑ የቤተክርስቲያን ችግር ሆኖ ይመጣል። ስለዚህ ወጣቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ወደ ትክክለኛው ነገር ማምራት አለባቸው።

እጮኛ የመምረጥን ጉዳይ በተመለከተ ወጣት ወንድሞችና እህቶች ስለዚህ ጉዳይ በእግዚአብሔር ፊት በግልፅ እንደሚቀርቡ ተስፋ እናደርጋለን። ጉዳዩን በተጨባጭ ማየት አለባቸው። በይሆናል ብቻ ማለፍ የለባቸውም። ነገሮችን በሀሳብ ብቻ መጨረስ የአንድን ሰው ልብና አዕምሮ በስሜት ሊያሸፍተው ይችላል። ረጋ ብሎ በተጨባጭ ማየትና ለነገሮች ሁሉ ትኩረት በመስጠት በእግዚአብሔር ፊት ማጤን ያስፈልጋል። በስሜት ወደሚገፋፋ ነገሮች ዘለው መግባት የለባቸውም። ከርስቲያን ጋብቻ ውስጥ ዘሎ ሊገባ ይችላል። ነገር ግን ዘሎ መውጣት አይችልም። እኛ ክርስቲያኖች በቀላሉ ተጋብተው በቀላሉ እንደሚፋቱ ዓለማውያን ዓይነት ባሕርይ ሊኖረን አይችልም፥ ዘለን መውጣት አንችልም። ስለዚህ ዘለህ ከመግባትህ በፊት በጥንቃቄ አስተውል።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ እርኅኘነትን በተመለከተ ጥቂት መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን አነሳለሁ። እነዚህም ከውጫዊ ማንነት ጀምረው ወደ ውስጥ ማንነት የሚዘልቁ ናቸው። ይህንም ያደረግኩት ወጣት ወንድሞችና እህቶች በፀጥታ በእግዚአብሔር ፊት አንድ በአንድ ያዩአቸዋል ከሚል ተስፋ ነው።

የተፈጥሮ ውበት

የያዕቆብና የራሔል ጋብቻ ከያዕቆብና ከልያ ይልቅ በውበት ላይ ተመስርቶ የተደረገ ነው። ማለትም የራሔልና የያዕቆብ ጋብቻ መሠረቱ የተፈጥሮ ውበት ነበር ማለት ነው። ስለዚህ የተፈጥሮን ውበት መንቀፍ የለብንም ። እርኅኛን ስንመርጥ ዝም ብለን ያገኘነውን ወንድም ወይም እህት እንመርጥም። አስተውሉ ወንድምና እህት ለመሆን የተፈጥሮ ውበት አያስፈልግም። በጋብቻ ለመጣመር ግን ብዙ ሁኔታዎች አብረው ይታሰባሉ። ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው ውበት ነው ። ዶክተር ቤቫን የተባሉት ሰው "የክርስቲያን ሚኽነሪ ኢሊያንስ" በተባለው ድርጅት ውስጥ ጌታ በታላቅ ሁኔታ የተጠቀመባቸው ሰው ናቸው። እርሳቸውም እንዲህ በማለት ተናግረዋል "ጌታ አንተን ለብዙ ወንድሞችና እህቶች ወንድም ወይም እህት ሊያደርግህ የተፈጥሮ ውበት ስፍራ የለውም፣ ነገር ግን እህት ወይም ወንድም እንድታገባ ሲያደርግ የተፈጥሮ ውበትም ሥፍራ አለው" ብለዋል። ስለዚህ አማኞች የተፈጥሮ ውበት እንደሚኖር ማወቅ አለባቸው።

እርኅኛ በምትመርጥበት ጊዜ ከዚያ ከመረጥከው ሰው ጋር አብሮ መሆንን የምትወድና የምትደሰትበት ሊሆን ይገባል። የሌላኛውን ወገን አብሮህ መሆን ታግሰህ የምትችለው ሳይሆን አብረህ መሆንህን የምትደሰትበት መሆን አለበት። የሌላው አብሮህ መሆን የማያስደስትህ ከሆነ መሠረታዊ ነገር ይጎድለዋልና ማግባት የለብህም። ከዚህ በተጨማሪ የሌላው ወገን አብሮህ መሆን የሚሰጥህ ደስታ ጊዜያዊ መሆን የለበትም። የሁልጊዜ መሆን አለበት፥ከሰላሳ ወይም ከሃምሣ ዓመት በኋላ በአንድነት መሆናችሁን የምትወደው ስለመሆኑ ሊሰማህ ይገባል ።

ጤንነት

1. ፍቅር ያሸንፋል

የአንድ ሰው የአካል ጉድለት በሌላው ሰው ታላቅ ፍቅር ሊሸነፍ ወይም ሊሸፈን ይችላል። እርግጥ ነው አንዳንድ ጊዜ የአካል ጉድለት ያለባቸውን ሰዎች ለማገልገል ካለ ታላቅ ፍቅር የተነሣ አንድ ሰው ሌላውን የአካል ጉድለት ያለበት ሰው ሊያገባ ይችላል። አንድ በእንግሊዝ

አገር የሚኖር ወንድም ሌላኛዋ እህት ዓይነ ስውር በመሆኗ ምክንያት ለመርዳት ሲል አግብቷታል። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሌሎች ተመሣሣይ ሁኔታዎች አሉ። ፍቅር ታላቅ በመሆኑ ምክንያት የአካል ጉድለትን አሸንፏል።

2. <u>የተለመዱ ሁኔታዎች</u>

ነገር ግን እንደዚያ ዓይነት ታላቅ ፍቅር በሁሉም ሰው ዘንድ አናገኝም። በአጠቃላይ አነጋገር ጉድለት ያለበት አካል የጋብቻን ስኬታማነት አደጋ ላይ ይጥለዋል። አንድ ሰው ሁል ጊዜ ቢታመምና ሌላኛው ወገን ብዙ መስዋዕት ቢከፍል ይህ የጋብቻን ብልፅግና ያናጋል።

በአካል ጉድለት ምክንያት አንድ ሰው ሁል ጊዜ ዕርዳታን የሚቀበል ከሆነ ይህ ሰው ራስ ወዳድና በቀላሉ ስሜቱ የሚነካ ወይም ሆድ የሚብሰው የመሆን እድሉ ሰፊ ነው። ራስ ወዳድ ሰው ሁል ጊዜ መቀበል እንጅ መስጠት አይችልም። ማለትም ይቀበላል እንጅ አይሰጥም። አካለ ጎደሎ ሰው ከራስ ወዳድነት ውጭም መረዳት እንዳለበት ያስባል ሊጎድልበትም ይቆጣል። እንግዲህ ከጊዜ ብዛት ይህ የራስ ወዳድነት መንፈስ እየታወቀ ሲሄድ ሌላኛው ወገን ደካማውን ሰው የመጥላትና የመናቅ ስሜት ያድርበታል። ወይም ተቀባዩ ራስ ወዳድ ካልሆነ ለሚደረግለት ነገር በጣም ሊሣቀቅ ይችላል። ይህም ራሱ ችግር ነው። ደካማው ሰው ሁል ጊዜ ርዳታን የሚቀበል ከሆነ ብዙ መስዋዕት በከፈለው በሌላኛው ሰው አመለካከት ሊዋጥ ወይም በቁጥጥር ስር ሊውል ይችላል። ይህ ደግሞ የተቀባዩ ሰው ቀኖች ይከብዱበታል።

ስለዚህ የምናገለግለውን ሰው እናስተውል። አንድ ሰው በፈታደኝ ነት መስዋዕትነት ሊከፍል ይችላል። እንደዚያም ሆኖ ብዙ ያደረገ መስሎት ሊሰማው ይችላል።የሰው ትዕግስት ወሰን አለው። አንዳንድ ጊዜ ብዙ በመስጠታችን ስጋችን ያሸንፈንና ትዕግስታችን ሊያልቅ ይችላል።ትዕግስት ተሟጦ ሲያልቅ ደግሞ የቤተሰብ ችግር ይጀምራል። አንዳንዴ ደግሞ ትዕግስታችን ባያልቅም እንኳ መስዋዕት ለማድረግ ፈቃደኛ የማንሆንበትና የምንጠነቀቅበት ጊዜ አለ ።

በእነዚህ ምክንያቶች የአካል ጤንነት ይህን ያህል ከፍተኛ ችግር ነው ባንልም በወደፊቱ የቤተሰብ ሁኔታ ላይ ግን ችግር ሊያመጣ ይችላል። በጋብቻ ጊዜ ችግር መስሎ ባይታየንም ከጋብቻ በኋላ ግን ራሱን የቻለ ችግር ሆኖ ብቅ ሊል ይችላል።

አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ አንድ በፅኑ የታመመ ባል አውቃለሁ። ሚስትም ቤተሰቡን ትንከባከባለች። ይህ ሁኔታ ግን ሊዘልቅ የቻለው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ለረጅም ጊዜ ሊዘልቅ አልቻለም። ሚስት ለአንድ

ወይም ለሁለት ወር ልትሰራ ትችላለች። ለሁል ጊዜ ግን አታደርገውም። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አይዘልቅም።

ጋብቻ የተሳካ እንዲሆን ሁለቱም ግለትም ባልና ሚስት ተመጣጣኝ ጤንነት ሊኖራቸው እንደሚገባ አምናለሁ። ከሁለት አንዳቸው በፅኑ የታመሙ መሆን የለባቸውም። አለበለዚያ ግን ልዩ ፈተና በሚገጥማቸው ወቅት ችግሩ ሊሸከሙት የማይቻል ሊሆን ይችላል።

የቤተሰብና የግለሰቡ የኋላ ታሪክ

ጋብቻ ከረጅም ጊዜ አኳያ በእርጋታ ሊታይ ይገባዋል። ስለዚህ የቤተሰብ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አንድ ሰው የሚያገባውን ሰው የቤተሰብ ሁኔታ ሊያጠና ይገባዋል።

የእግዚአብሔር ሕግ እንዲህ ይላል "...በሚጠሉኝ እስከ ሶስተኛ እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወዱኝ ትዕዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና "/ዘፀ 20 ፥56/።

ብዙዎች ስርዓት ያጣና የተበላሸ ኑሮ በወጣትነታቸው ይኖራሉ። የዚህ ምክንያቱ የእነርሱ ወላጆች ወይም አያቶች አስቀድመው ያንን ዘር ስለዘሩባቸው ነው / ሆሴ 8፥7/ በነፋስ የሚዘራ ሰው መረን የወጣና ግብረገብነት የጎደለው ኑሮ ይኖራል። እንደዚያ ዓይነት ሰው ምን አልባት ንስሐ ገብቶ አዲስ ሕይወትን አግኝቶ ይሆናል። ነገር ግን ይህ ሰው ለመዳን ብቁ ቢሆንም እንኳ ቀደም ሲል ካሳለፈው ሕይወት የተነሳ ለማግባት ብቁ ላያደርገው ይችላል። እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ብሎታል፣ አዲስ ሕይወትም ሰጥቶታል። ነገር ግን ከዚህ ሰው ልቅ ሕይወት የተነሳ የእርሱ ልጅ በቀላሉ ላይድን ይችላል። ከዚህ ሰው ያልተቆረጠ መጥፎ ሕይወት ወደ ሚቀጥለው ትውልድ ሊሸጋገር ይችላል።ካሳለፈው ሕይወት የተነሳ ከመንፈሳዊ ነገር ይልቅ ሥጋዊ ነገርን የሚናፍቅ ከሆነ በሚወልዳቸው ልጆች ይህ ምኞት ሊቀረጽና ዓለምን የበለጠ ሊወዱ ይችላሉ። ስለሆነም በአለፈው ሕይወታችን ምክንያት የኃጢአትን ዘር በልጆቻችን ሕይወት መትከል ይቻላል፤ ዳግም መወለድን ግን ለዘር ማውረስ አይቻልም። ስለዚህ የሚመጣው ትውልድ የበለጠ ኃጢአተኛና ሕግን የማያከብር እየሆነ ሊመጣ ይችላል። ይህም ለወላጆቹ የሐዘን ምክንያት ይሆናል። ምን አልባት አንዳንድ ሰዎች እንዴት ዳግም የተወለዱ ሰዎች እንደዚህ ዓይነት አስቸጋሪ ሰዎች ወለዱ ብለው ሊጠይቁ ይችሉ ይሆናል። ከአለፈው ሕይወታችን የተነሳ አሁን የሚያንፀባርቋቸው መጥፎ ምግባሮች የዚህ ምክንያቱ ወደ ሁለተኛውና ወደ ሶስተኛው

ትውልድ ሕይወት ተሸጋግረው ሊሆን ስለሚችል ነው። ነፋስን የዘራ አውሎ ንፋስን ያጭዳል። ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳልና። እንደዚህ ዓይነቱ መዝራትና ማጨድ በአንድ ሰው ቤተሰብ ላይ በጣም አደገኛ ልጆችን ንስሐ ለማስገባት ለቤተክርስቲያን አስቸጋሪ የሆነ ትውልድን ሊያመጣ ይችላል። በእርግጥም ይህ የከፋ ችግር ነው። እግዚአብሔር ከቀለለበት ቤተሰብ የመጣ ሰው በጌታ አምኖ ቢሆንም ካለፈው ሕይወቱ የተነሳ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ላይፈራ ይችላል። ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ጊዜ ውድ የሆነውን ሳይሆን ጊዜ ማሳለፊያ ሲያጣ ብቻ ይሆናል። ይህ በልጆች ሕይወት ይበቅላል።

ነገር ግን ችግር ያለባቸውና አስቀድመው ያገቡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ምህረት መፈለግ አለባቸው። ከዚህ ዓይነቱ ሕይወት ነፃ እንዲወጡ እግዚአብሔርን መለመን ይገባቸዋል። እንዲህ ሲያደርጉ እነሱም ሆኑ ልጆቻቸው የጌታ ነገር ስለሚፈልጉ አውሎ ንፋስ ከማጨድ ይድናሉ። ስለዚህ ይህ ሰው ከቤተሰቦቹ ከወረሰው ሕይወት የተነሳ ለክርስቲያናዊ ጋብቻ በቁ ነው ወይ? ይህን ጥያቄ መመለስ መቻል አለብን።

አንድ የምዕራባውያን አባባል አለ "እኔ ያገባሁት እሷን እንጂ ቤተሰቦቿን አይደለም "ይህ በእውነቱ ትክክለኛ አባባል አይደለም። አንዲት ልጃገረድ ስታገባ ቤተሰቦቿም አብረው እንደሚመጡ የታወቀ ነው። ስለዚህ ከማግባትህ በፊት ጥንቃቄ አድርግ።

1. <u>የቤተሰብ ተፅዕኖ</u>

አንድ ሰው ይብዛም ይነስም የቤተሰብ ተፅዕኖ አለበት። አንድ ሰው ለማግባት ሲያስብ የሌላውን ሰው የቤተሰብ ሥነ ምግባር ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ ማየት አለበት። ምግባራቸው የሚደነቅ ነው ወይ? ያን ደረጃስ እንዴት ነው የሚጠብቁት? ወንዶች ለሴቶች ሴቶችም ለወንዶች ያላቸው አመለካከት እንዴት ነው? አንድ ሰው እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በማየት የወደፊት ቤቱ ምን እንደሚመስል በዚህ መገመት ይችላል።

አንድ ለሃያና ከዚያም በላይ ለሆኑ ዓመታት የቤተሰቡን ትምህርት ሲቀስም የኖረ ሰው ወደ አዲሱ ቤቱ ሳያውቀው ያደገበትን ቤተሰብ ባህርይ ይዞ ሊመጣ ይችላል። ይህ ሰው በአደገበት ቤተሰብ አኗኗር የማይደሰት ቢሆንም እንኳን ሳያውቀው ይዞት ይመጣል። ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ አሮጌው ኑሮው ይበቅላል። እርግጥ አስር ሰዎች ቢኖሩ አስሩም የዚያን ቤተሰብ ባሕርይ ይይዛሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን በሰባት ወይም በሰምንቱ ላይ ይከሰታል። የአሮጌው ቤተሰብ ባሕርይ

ሁሉም በአንድ ጊዜ ባይገለፅም ቀስ በቀስ ግን መውጣቱ አይቀርም። ስለዚህ ወጣት ወገኖች የጋብቻቸውን ስኬታማነት ለመጠበቅ እነዚህን ነገሮች ማጥናትና በጥንቃቄ አንድ በአንድ መዝነው ማወቅ አለባቸው።

በቤተሰብ ውስጥ አባትዮው ሁል ጊዜ ልጆቹን በኃይል የሚያዛቸውና የሚጫናቸው ከሆነ በዚያ ቤተሰብ ውስጥ ያለ ልጅ ፍቅር የማያውቅ እንደሚሆን ግልፅ ነው። የፍቅር ሰው አይሆንም። ነገር ግን ሰላም ባለበት ቤተሰብ እና ወላጆቹ በፍቅር የተሞሉ ከሆነ በዚያ ቤት ያለ ልጅ በቀላሉ ከሌሎች ጋር የሚግባባ ይሆናል። እናትና አባት ጥብቅ ከሆኑበት ቤተሰብ የሚመጣ ልጅ ደግሞ ለሃያ ዓመትና ከዚያ በላይ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ስለሚቆይ አሳበ ግትር ይሆናል። ስሜቱ ወደ ወላጆቹ ሳይሆን ወደ ራሱ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ፍቅሩን የመግለጽ ችግር አለበት። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በሚስትም ላይ ይገለፃል። ከአሥር ሰዎች ውስጥ በሰባቱና በስምንቱ ላይ የቤተሰብ ሁኔታ በሁለተኛው ትውልድ ላይ ይገለፃል ይታያልም።

2. <u>እናት</u>

"አንድ ሰው ልጅቱን ሊያገባ ከፈለገ እናቷን ይመልከት" ይህ አባባል ከሞላ ጎደል እውነት ነው። እናቷ አባቷን እንዴት እንደምትን ከባከበው ፀማየት ልጅቱ እንዴት እንደምትንከባከብህ ማወቅ ትችላለህ። ልጅቱ የእናቷን ድርጊትና ኑሮ ከሃያ ዓመት በላይ አይታለች። ስለዚህ ላንተም የምታደርገው ይህንኑ ነው። እናቷ ለአባቷ በየቀኑ የምታደርገውን ለብዙ ዓመት ያየች ልጅ ከዚያ ውጭ ለማድረግ ይከብድባታል። እንደዚሁም ሁሉ አባትዮውን በማየት ልጅዮው እንዴት ሚስቱን እንደሚንከባከባት ለማየት ትችላለህ።

ለምሣሌ አንድ ጨቅጫቃ የሆነ ሰው ለተወሰነ ጊዜ በንግግሩ ጨዋ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህ ሰው ወደ አንድ ግትር ፀባይ ወዳለው ቤተሰብ ቢመጣ ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ ጨቅጫቃ ባህርይው ሊገለፅ ይችላል። ሌላ ደግሞ ቁጥብና ከጨዋ ቤተሰብ የመጣ ሰው በንግግሩና በሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ጠንቃቃና ሰው አክባሪ ይሆናል። ይህ ሰው ቢያንስ ፀቡ ትክክል እንዳልሆነ ያውቃል። ለዚህ ሰው ስድብና ድብድብ ረጅምን ተራራ እንደመውጣት ይሆንበታል። ነገር ግን ድብድብና ስድብን የዕለት ተግባራቸው ካደረጉ ቤተሰቦች የመጣ ሰው ታሪኩ የተለየ ነው። ምናልባት ዛሬ በጣም ጨዋነት ቢያሳይ ይህ ባህርይ ግን ፀንቶ የሚቆይ ሳይሆን ጊዜያዊ ነው። አንድ ቀን ካደገበት ቤት የተማረው ባህርይ ፈንድቶ ይወጣል።ለዚህ ሰው ስድብና ድብድብ ቀላል ነው፣ አይከብደውም።

በእነዚህ ምክንያቶች አንድ ሰው ከማግባቱ በፊት የሚያገባውን ሰው ቤተሰብ ታሪክ ማጥናት አለበት። እንደሚታወቀው ከአሥር ልጆች ውስጥ ሰባቱ ወላጆቻቸውን ይመስላሉ። ቤተሰቡን ትወደዋለህን? ያን ቤተሰብ ከወደድህ ያንተም የወደፊት ቤት ከሞላ ጎደል ያንን ይመስላል። ያን ቤተሰብ የማትወደው ከሆነ ግን የምታገባው ሰው ከዚያ ቤተሰብ ልዩ ይሆናል ብለህ አትጠብቅ። ከዚያ ልዩ መሆን ቀላል አይደለም።

3. <u>መላ ቤተሰብ</u>

አስተውል አንድ ሰው የሚናገረውና የሚያስተምረው ከዚያ ሰው አካሄድ ሊለይ ይችላል። አንድ ሰው መጣላት ትክክል እንዳልሆነ ሊነግርህ ይቻላል። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ራሱ ሲጣላ ታገኘዋለህ። ይህን ባሕሪውን ለመለወጥ ቀላል ሆኖ አያገኘውም። ስለዚህ ወንድሞች እህቶችን ስታገቡ የእርሷን መላ ቤተሰብ እንዳገባችሁ እወቁ። እህቶችም ወንድሞችን ስታገቡ የእርሱን መላ ቤተሰብ እንዳገባችሁ እወቁ። ያገባችሁት አንድ ሰው ቢሆንም በትክክል ግን ያገባችሁት መላ ቤተሰቡን ነው።

<u>ዕድሜ</u>

1. <u>የአካል መብሰል</u>

በአጠቃላይ አነጋገር ሴቶች ከወንዶች ቀድመው ይደርሳሉ፣ እንዲሁም ደግሞ ቀድመው ያረጃሉ። ሴቶች አብረዋቸው ከተወለዱ ወንዶች አምስት አመት ቀድመው ያድጋሉ፣ እንዲሁም አስር አመት ቀድመው ያረጃሉ። ስለዚህ በጋብቻ ውስጥ አካላዊ እድገትን በተመለከተ ሴቷን የሚያገባ ሰው ከአምስት እስከ ሰምንት ዓመት የሚበልጣትን ሴት ቢያገባ ይመረጣል።

2. <u>የአዕምሮ መብሰል</u>

በሌላ በኩል ደግሞ የአዕምሮ እድገት አለ። አንዳንድ ሰዎች በአካል አድገው በአዕምሮ ግን ገና ልጅ ይሆናሉ። አንድ ሰው በአካል ሰላሳ ዓመት በአዕምሮው ደግሞ የሃያ ዓመት ዕድሜ ያለው ሆኖ ሊገኝ ይችላል። በዚህ ምክንያት ለማግባት በአዕምሮው የበሰለ ወንድም በአካል ትልቅ በአዕምሮ ግን ወጣት የሆነች ሴት ለማግባት ይችላል ።

እንግዲህ ውሳኔው የሚያርፈው እንደ አንተ አመለካከት ነው። ምናልባት አንተን የሚስብህ አካላዊ እድሜ ወይም አዕምሮአዊ ብስለት ሊሆን ይችላል። አካላዊ እድሜን በተመለከተ ወንዱ ከሴቷ ቢሸመግል ይመረጣል። ነገር ግን የአዕምሮን እድገት በተመለከተ ሴቷ ከወንዱ

ብትበልጥም ችግር የለውም። እንግዲህ ይህ እያንዳንዳቸው ለራሣቸው የሚወስኑት ነው።

ባህርይ ፣ ዝንባሌና ዓላማ

ቀደም ሲል ያየናቸው ነገሮች ከአካል ጋር የተያያዙ ናቸው። ከአሁን ጀምሮ ደግሞ ከባሕርይ ጋር በሚገናኙ ነገሮች ላይ እናተኩራለን።

ለጋብቻ ስኬታማነት የተፈጥሮ ውበት ብቻውን በቂ አይደለም። የባህርይ፣ የዝንባሌና የዓላማ መጣጣም ያስፈልጋል። የሁለት ሰዎች ባሕርይና ዝንባሌ ከተራራቀ ያቤተሰብ ቀስ በቀስ ሰላሙን ያጣል። ባልና ሚስትም ይሰቃያሉ። ስለዚህ ወጣቶች አካላዊ ውበት ጊዜያዊ፣ ባህሪ ግን ዘለቄታዊ መሆኑን ማወቅ አለባችሁ።

በማያምኑ ሰዎች መካከል የሚታየው ፍቅር አብዛኛውን ጊዜ የተፈጥሮ ውበትን መሠረት ያደረገ ነው። እዚህ ላይ ፍቅር ስንል ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ዓይነት ማለት አይደለም። በተፈጥሮ ውበት ፍቅር አለ። ነገር ግን የተፈጥሮ ውበት ፍቅርን በሙሉ አይገልፅም። ፍቅር የተፈጥሮን ውበት ያጠቃልላል። እንዲሁም የባህርይ መጣጣምንም ይጨምራል። ስለዚህ ፍቅር ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን ይይዛል። እነዚህም የውበት፣ የባህርይና የዝንባሌ መጣጣም ናቸው።

አንድ ሰው ውበት ስላለው ያፈቀርኸው ሊመስልህ ይችላል። ነገር ግን ይህ ሰው የሚያደርገውን ላትወደው ትችላለህ። የሚያደርገው ሁሉ አንተ ከምትፈልገው ሊለይ ይችላል። እርሱም አንተ የምትወደውን ላይወድ ይችላል። አንተም እርሱ የሚወደውን ላትወድ ትችላህ ። እንግዲህ ይህ የሚያሳየን የባሕርይ መለያየትን ነው።

1. ፍቅር

ለምሳሌ ከሁለት አንዳቸው ሰዎችን በጣም ሊወዱ ይችላል። ይህም ሰው ማንኛውንም ሰው በትህትና፣ በፍቅርና በአክብሮት ያስተናግዳል። ነገር ግን ሌላኛው ወገን ለሰዎች ቀዝቃዛና ግዴለሽ፣ ፍቅርና ርህራሄ የጎደለው ሊሆን ይችላል። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ቢገናኙ ወዲያውኑ በሁለቱ በኩል ችግር ሲፈጠር ታያለህ። በሁለቱ መካከል የባህርይ ግጭት አለ። እንግዲህ ሰዎችን የሚያፈቅሩ፣ በትህትናና በፍቅርም የሚንከባከቡ ሁለት ሰዎች ቢጋቡ ሁለቱም ለሰዎች ትልቅ ጥንቃቄ ለማድረግ ዝንባሌ ያላቸው ሆነው ታገኛቸዋለህ። እንደነዚህ ያሉትም ጋብቻን ቀላል ሆኖ ያገኙታል። ልክ ወደ ምዕራብ በሚፈስ ወንዝ ላይ ወደ ምዕራብ የመጓዝን

ያህል ቀላል ይሆንላቸዋል። ይህም ወንዙ ወደ ሚሄድበት አቅጣጫ እንደመጋለብ ማለት ነው። ነገር ግን ቁዝቃዛና ምንም ስሜት የሌለው ሰው ብታገባ አንተ ወደ አንድ አቅጣጫ ስትሰብ እርሱ ደግሞ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይጎትታል ቢሆንም ግን የትዳር ጓደኛህን መሸከም እንዳለብህ ይሰማሃል፣ ያገባኸውም ሰው አንተን ችሎ ለመታገስ ይሞክራል። ስለዚህ አንዱ የሌላውን ስስታምነት ሲታገስ ሌላኛው ደግሞ የዚያኛውን ለጋስነት ይታገሣል፤እንግዲህ ይህ በትዳር ውስጥ ጣዕም ያለው ነገር አይደለም።

2. ርህራሄ

አንዳንድ ሰዎች ሰውን የሚያፈቅሩ ብቻ ሳይሆን ሩህሩህም ናቸው። ርህራሄ ማለት የሌላውን ጉዳት አለመውደድ፣ ሌላው ሰው እንዳይጎዳ ማሰብ ነው። ወይም የሌላው ጉዳትና ችግር የሚሰማው ማለት ነው። ስለዚህ ሕይወት ትርጉም ያለው የሚሆነው አንድ አይነት ባሕርይ ከአንተ ጋር ያለውን ሰው መርጠህ ካገባህ ነው። ሁለታችሁም ሩህሩሆችና ለሰው አሳቢ ከሆናችሁ የሌላውን ሰው ስሜት በመጠበቅ ትደሰታላችሁ። ሌላውን ሰው በማዘን ደስታ አይኖራችሁም። ሰውን ማሳዘን ወንዙ ወደ ምዕራብ እየወረደ እናንተ ግን ወደ ምስራቅ የመጓዝን ያህል ይሆንባችኋል።እንግዲህ ተቃራኒ ባሕርይ ያለውን ሰው ብታገቡ ምን ይመጣል? ከፍተኛ ችግር ይገጥማችኋል። ለምሳሌ አንተ ከሩህሩህነትህ የተነሳ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለድመቶችና ለውሻዎች ጭምር የምትኖር ብትሆንና ያገባሃው ሰው ግን ለሰውም ለእንስሳም ፍቅር ባይኖረው ይህ በቤተሰብ ውስጥ ትልቅ ችግር ይፈጥራል። ሁለታችሁም በተቃራኒ አቅጣጫ ነው የምትገዙት። እንዲህ ከሆነ ትዳር ይናጋል።

3. ልግስና

በጣም ለጋስ የሆነ ሰው ገና ወንድሞችና እህቶች ይመጣሉ በማለት ያለውን ሁሉ ጠረጴዛ ላይ ደርድሮ ይጠብቃል። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ሰው በተቃራኒው ወዳጆች የበሉትን እያንዳንዱን ምግብ የሚቆጥረውን ሰው ቢያገባ ጥሩ የቤት ሁኔታ አይኖረውም። ይህ ዓይነቱ ችግር የባህርይ ጉዳይ ነው። አንዳንድ ሰዎች በባህርያቸው ሰዎች ምግባቸውን ሲበሉ ይሰማቸዋል፣ ደስ አይሰኙም፣ አይወዱም። አንዳንዶቹ ደግሞ ሆን ብለው ጥሩውን በመደበቅ ያልሆነውን ለእንግዶች ያቀርባሉ። ይህም የባህርይ ችግር ነው።

4. ግልጽና ድብቅ

አንዳንድ ወንድሞች በተፈጥሮአቸው ግልፅ ናቸው። የሚያውቁትን ሳይደብቁ መናገር ይወዳሉ። አንዳንድ እህቶች ደግሞ

በተፈጥሮአቸው ስጉና ጠንቃቃ ናቸው። ስለሆነም አብሮአቸው የሚኖር ሰው በአነጋገሩ ጠንቃቃ እንዲሆን ይፈልጋሉ። በዚህ መካከል የባህርይ ግጭት ይፈጠራል። የእነዚህን ሰዎች ባህርይ ትክክል ነው ወይንም ስህተት ነው ለማለት አንችልም። በዚህ ውስጥ ሕሊናቸውን የሚወቅሳቸው ነገር የለም። የዚህ ችግር ባህርይ ነው። አንደኛው በጣም ስጉ ስለሆነ ማንኛውንም ነገር ይደብቃል፣ አይናገርም። ሌላኛው ደግሞ በግልጥ ሁሉን ነገር ማውጣት ይፈልጋል ። ይሁን እንጅ የሁለቱም ባሕርይ መልካም ነው። ስለዚህ ጠንቃቃውም ግልፁን አይንቀፍ፣ ግልጡም ጠንቃቃውን አይንቀፍ። ወደ ትዳር ስንመጣ ግን ግልፁ ሰው እርምጃው በድብቁ ሰው እየተጎተተበት፣ ድብቁ ደግሞ በግልፁ ሰው ሁሉ ነገር ፈጥኖ እየወጣበትና ለነፋስ የተሰጠበት ሊመስለው ይችላል። በዚህ ምክንያት ሁለቱም የባህርይ አለመጣጣም ይገጥማቸዋል። ይህም ሥቃይ ውስጥ ሊከታቸው ይችላል። ስለዚህ በባህርይ የሚመስላቸውን ሰው ቢያገቡ ከዚህ ዓይነቱ ችግር ያመልጣሉ።

5. <u>አውጥቶና አውርዶ የሚያደርግና በስሜት ተገፋፍቶ እርምጃ የሚወስድ</u>

አንዳንድ ሰዎች አንድን ነገር የሚያደርጉት አስበው ነው። እያንዳንዱን ነገር በጥንቃቄና በጥልቀት ያስቡበታል። ሌሎች ደግሞ ነገሮችን የሚያደርጉት ምንም ዓይነት ማብራሪያ እንኳ ሳይጠይቁ ነው። እነዚህ ሰዎች ቆም ብለው የሚያስቡት ነገሮችን ካደረጉ በኋላ ነው። እንግዲህ ይህ የባህርይ ችግር ነው። ስለዚህ አንዱ በሌላው ላይ አይፍረድ። ይልቁንም አስቦ የሚያደርግ ሰው አስባ የምታደርግ ሚስት ይፈልግ። ይህ አብሮ የመኖርን ሕይወት ቀና ያደርገዋል ።

6. <u>ተጠንቅቆ መናገር</u>

አንዳንድ ሰዎች ለሚናገሩት ነገር ጠንቃቃ ናቸው። እያንዳንዱ ቃል ለትክክለኛው ነገር ብቻ መዋል አለበት ይላሉ። ለሚናገሯት ቃል ይጠነቀቃሉ። ሌሎች ግን ግድ የላቸውም። ብዙ አይጠነቀቁም። እነዚህ ሰዎች ግድ የለሽ ላለመሆን ፈልገው ሳይሆን እንዲሁ ሲናገሩ ተጠንቅቀው አይናገሩትም። ይህም የባሕርይ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ጠንቃቃው ሰው ሌላውን አልተጠነቀቀም ብሎ የማያስፈልግ ወቀሳ ሊያደርግበት ወይንም ጨርሰህ ባትናገር ይሻላል ብሎ መንቀፍ የለበትም። እርግጥ ነው በዓለም ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ቃል በጥንቃቄ ሊነገር ይገባል። ነገር ግን ለአንዳንዶች ምንም ያህል ቢጠነቀቁ ከተናገሩት ውስጥ የሚጠነቀቁበት ከሃያ ዓረፍተ ነገር አይበልጥም። ስለዚህ የባሪይ አለመጣጣም ትልቅ ችግር ነው። ስለሆነም እነዚህ ሰዎች እንደየ ባህርያቸው የሚስማሟቸውን ፈልገው ቢያገቡ መልካም ነው።

7. ፈጣንና ዘገምተኛ

አንዳንድ ሰዎች ፈጣን ባህርይ ሲኖራቸው ሌሎቹ ደግሞ ዳተኛ ባህርይ አላቸው። በእነዚህ በሁለቱ ውስጥ ምንም ዓይነት ስህተት የለም። ስህተት ስላልሆነም ሀሊናቸውን የሚወቅሳቸው ነገር አይኖርም ። ልዩነቱ የባህርይ ጉዳይ ነው። ነገር ግን አንዲት ፈጣን እህት በጣም ዳተኛ የሆነ ወንድም ብታገባ በቤተሰባቸው ውስጥ ችግር እንደሚፈጠር ጥርጥር የለውም÷ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ ይህን የባሕሪ ችግር ወደ ከፋ ደረጃ ሊያመጡት ይችላሉ። የየራሣቸውን ልዩ ባህርይ ለማጉላት ይሞክራሉ። ሁል ጊዜ ቤቱ መቀመጥ የሚወድ ባል አጋጥሞኛል። ነገር ግን ይህ ሰው እየዞረች ሰዎችን መጠየቅ የምትወድ ሚስት አገባ። እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን በሻንጋይ ውስጥ ጥቂት አውቃለሁ። ባልዮው ሚስቱን ተክትሎ በየሰው ቤት መዞር የማይቻል ሆኖ አገኘው። ስለሆነም የወሰደው አማራጭ ቤት ቀርቶ ሚስቱ እስክትመጣ ቤት ይጠብቅ ጀመር። ይህን ሁኔታ ለጥቂት ጊዜ ታግሶ ቆየ። ለሁልጊዜ ግን መታገስ አልቻለም። ቤት ሲመጣ ብዙ ጊዜ አያገኛትም። ይህ ችግር ከጋብቻ በፊት በንቀት ታይቶ የታለፈ የባህርይ ጉዳይ ነው። በመሆኑም በፊት ቀላል የሚመስለው ችግር አሁን የማይቻል ሆነ፣ ቤተሰቡንም አናጋው።

8. ንፁህ ወይም ዝርክርክ

በጣም ንፅሕናን የምትወድ አንዲት እህት አውቃለሁ። ሁልጊዜ ባሏን እየተከተለች እያንዳንዷን ነገር ታፀዳለች። ነገር ግን ባልየው ግድ የለውም። አንድ ቀን ልጎበኛቸው ቤታቸው ስሄድ ባልየው ትራሱን ወለል ላይ ወርውሮና ወንበሮችን ሁሉ አመሰቃቅሎ አገኘሁት። እኔም ለምን እንዚህን ነገሮች እንዳደረገ ጠየቅሁት። እርሱም ሲመልስልኝ ዛሬ ባለቤቱ ወላጆቿን ልትጠይቅ በመሄዷ ምክንያት እስክትመለስ ድረስ እንዲሁ ቢቆይ ችግር እንደማይሆንበት ነገረኝ። ሁል ጊዜ እርሱን እየተከተለች እያንዳንዷን ነገር ስለምታፀዳ እንደሚፈራትና ጥንቃቄ እንደሚያደርግ ግን በመሄዷ ምክንያት ነፃነት በማግኘቱ ሁሉ ነገር ተዝረክርኮ ቢቀመጥ ለእርሱ ችግር እንዳልሆነበት ነገረኝ። እንግዲህ ይህ የባህርይ ጉዳይ ነው። ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ነገሮች ከጋብቻ በፊት ቀድመው ሊጠኑ ይገባቸዋል። በባህሪ የማይጣጣማችሁ ከሆነ ያን ሰው አታግቡት።

9. ተመሳሳይ ባህርይ

ፍቅር ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን እንደሚይዝ ማወቅ አለብን። እነዚህም የተፈጥሮ ውበትና የባህርይ መጣጣም ናቸው። እነዚህንም ቀደም ሲል አንስተናቸዋል። ስለዚህ እጮኛ በሚመረጥበት ጊዜ ከርስቲያን መምረጥ ያለበት የተፈጥሮ ውበትን ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር

ተመሣሣይ ባሕርይ ያላቸውንም ጭምር መሆን አለበት። በውበቷ ስለተማረከህ የባሕሪዋን ነገር ችል አትበለው።

ሻንጋይ ውስጥ ሁል ጊዜ የሚጣሉ ባልና ሚስቶች አጋጥመውኛል። እኔም ባልዮውን በመጀመሪያ ለምን አገባሃት ብየ ጠየቅሁት። እርሱም ሲመልስልኝ፡- በመጀመሪያ ባያት ጊዜ በሁለት ‘ዮቋቁር ዓይኖቿ እንደተማረከ ነገረኝ። እንግዲህ ይህ የተፈጥሮ ውበት ነው። ነገር ግን ከጋብቻ በኋላ እነዚያ ጥቋቁር ዓይኖች ተረሱ። አሁን እርሱ የሚያስታውሰው እርሱ ፀጥታ ሲፈልግ እርሷ በሳቅ መደሠቷን ነው። እርሱ ቀስ ብሎ ሲመልስ እርሷ ፈጥና ታደርጋለች። ስለዚህ አስተውል፣ የባህርይ ችግር ዘለቄታ ያለው ችግር ነው።

ስለዚህ ወንድሞችና እህቶች እጮኛ ሲመርጡ የተፈጥሮን ውበት ብቻ ማየት የለባቸውም። የተፈጥሮ ውበት ሊኖር ይገባል፣ ነገር ግን እርሱ ብቻውን በቂ አይደለም። የባህርይ መጣጣም መኖሩንም ማስተዋል አለባቸው። የተፈጥሮ ውበት ፈጥኖ ይጠፋል። የተፈጥሮ ውበት እንድታገባ ቢገፋፋህም ጋብቻህን ግን እንዲዘልቅ አያደርገውም። ወደ ጋብቻ እንድትጓዝ በቅድሚያ ሊያነሳሳህ ይችላል። ነገር ግን ጉዞህ እንዲቀጥል የማድረግ ኃይል የለውም።

10. <u>የመንግስተ ሰማያት ወይም የገሃነመ እሳት ምሳሌ ስለመሆኑ</u>

እንዲህ የሚል አንድ አባባል አለ፡- ሰው ሁለት መንግስተ ሰማያት ወይም ሁለት ገሃነመ እሣት ሊገጥመው ይችላል ይባላል። ደስተኛ ቤተሰብ መንግስተ ሰማያትን የሚመስል ነው። ችግር ያለበት ቤተሰብ ግን ገሃነመ እሳትን ይመስላል። የማያምን ሰው ሁለት ገሃነመ እሳት ሊገጥመው ይችላል። በገሃነመ እሳት ኖሮ ከሞተ በኋላም በገሃነመ እሳት ለመኖር ይሄዳል። ክርስቲያን ግን በቤተሰቡ አለመጣጣም ቢገጥመው እንኳ ዛሬ የገሃነም ኑሮ ቢኖርም ወደፊት ግን በመንግስተ ሰማያት ሊኖር ይሄዳል። ወይም ቤተሰቡ መልካም ከሆነ በምድርም መንግስተ ሰማያትን የመሰለ የጋብቻ ሕይወት ቀምሶ ወደ መንግስተ ሰማያት ይሄዳል።

ከማንም ሰው ጋር የምትጣላ ሚስት ያለው ወንድም አውቃለሁ ሲያዩአት በጣም መንፈሣዊና በሚገባ መፀለይም የምትችል ነች። ነገር ግን አመሏ ሲነሣ ማንም ከንግግሯ ሊመልሣት የሚችል ሰው የለም። ሁል ጊዜ ከጎረቤቶቿ ጋር ትጣላለች። ባለቤቷም እርሷ ስለፈፀመችው ነገር ሁል ጊዜ ይቅርታ ይጠይቃል። ወደ ቤቱ ሲመለስም ከጎረቤት ወይም ከሌላ ሰው ጋ ተጣልታ እንደሆነ በመጠየቅ ችግሩን ያስተካክላል። የሚገርመው ግን

ሁል ጊዜ የምትጣላ መሆኑ ነው። ነገር ግን ያ ወንድም ፀጥ ያለች ሚስት አግብቶ ቢሆን ኖሮ ቤተሠባቸው ብዙም ባልተረበሸ ነበር።

11. ሌላውን መቀበል

ብዙ ሰዎች ያንድን ሰው ባህርይ መለወጥ ይቻላል የሚል የተሳሳተ አመለካከት አላቸው። ይህ ግን ሊሆን አይችልም። መንፈስ ቅዱስ ራሱ የሰዎችን ባሕርይ ለመለወጥ ረጅም ጊዜ ይወስድበታል። ታዲያ አንተ ይህን የማይቻል ተግባር ይሳካልኛል ብለህ ታስባለህ? አስተውል ጋብቻ የአንድን ሰው ባህሪ የወለወጥ ኃይል የለውም። ብዙ ወንድሞችና እህቶች ከሌላው ሰው ጋር የባሕርይ ልዩነት እንዳላቸው አውቀው ይለወጣል በሚል ተስፋ ይጠብቃሉ። ነገር ግን የሚጠበቀው ለውጥ አይመጣም። ስለዚህ እያወቅህ ከገባህበት ይህ ባሕርይ እንደማይለወጥ አውቀህ ተስፋ ቁረጥ። እኔ እስካሁን ድረስ ባል ሚስቱን ሲለውጥ ወይም ሚስት ባሏን ስትለውጥ አላየሁም። በአብዛኛው በጋብቻ ውስጥ የምታገኘው መልካም ሆኖ የተሠራን እንጂ መልካም ለመሆን የሚሠራን ሰው አይደለም። አሁን ያገኘኸው ወንድም ወይም እህት ወደ ፊትም ያው ራሱ ነው። ስለዚህ ከማግባትህ በፊት የዚያን ሰው የአሁን ሁኔታ ተመልከተህና አጥንተህ የሚስማማህ ወይም የማይስማማህ መሆኑን እወቅ። ከጋብቻ በኋላ ግን የዚያን ሰው ባህርይ በመለወጥ የሚስማማኝን በሕርይ አገኛለሁ ብለህ አትጠብቅ፣ አታስብ።

12. ማስጠንቀቂያ

ከአሥር ዓመታት በላይ በሻንጋይ ስሠራ ሩቡን የአገልግሎት ዘመኔን ያሳለፍኩት የቤተሰብ ችግሮች በማቃለል ነበር። ከዚህ ልምድ እንዳየሁት የተለያየ ባሕርይ ያላቸው ሰዎች በአንድ ላይ እንዳይጣመሩ በጥብቅ አስጠነቅቃለሁ። ሳይጣጣሙ መጋባት ለባል ፣ ለሚስትና ለልጆች ጥሩ አይሆንም። እንደዚያ ባለ ጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ ልጆች አማኝ ነታቸው አይፀናም። ከማን ጋር እንደሚቆሙ አያውቁም። ይህ ደግሞ ደህንነታቸውን እንኳ ሣይቀር ስጋት ላይ ሊጥለው ይችላል።

ድካም

ቀደም ሲል ያየናቸው ጉዳዮች የሕሊና ወቀሳ የሌለባቸው የባህርይ ልዩነቶችን ብቻ ነው። አሁን ደግሞ የሰዎችን ድካም እንመለከታለን።

1. የሕሊና ወቀሳ የሚያመጣ

ድካም ምንድን ነው? አንዳንድ ሰዎች ሰነፎች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ትጉዎች ናቸው። ትጋት ጥሩ ምግባር መሆኑን ስንፍና ደግሞ ድካም መሆኑን እናውቃለን። አንዳንድ ሰዎች ቃልን ሲናገሩ በትክክል እንደሚገባ ይጠቀማሉ። ይህ በእውነት ጥሩ ምግባር ነው። ነገር ግን አንዳንዶች በንግግራቸው ጠንቃቃ አለመሆን ብቻ ሳይሆን በሚሉት ነገር ላይ ጥቂት ቃላት ጨምሮ መናገር ይወዳሉ ፣ ውሸትን ይናገራሉ። ይህ ድክመት ነው። አንዳንዶች ቁጥብ ከንፈር አላቸው። ብዙ መናገር አይወዱም። ይህም መልካም ነው። ነገር ግን አንዳንዶች መተቸትና መናገር ይወዳሉ። ይህ ደግሞ እንደ ጥሩ ምግባር ሊወሰድ አይችልም። ይህ ድክመት ነው። ወሬን ማናፈስ ከባሕርይ ችግር በላይ ስለሆነ የሕሊና ወቀሳ ይጨምራል። የሕሊናን ወቀሳ የሚጨምር ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መስተካከል ያለበት ድክመት ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ነገሮች ወዲያውኑ ሲያደርጉ ሌሎች ግን ዘግይተው ያደርጋሉ ይህ የባሕርይ ችግር ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ቶሎ ማድረግ ለሚገባው ነገር ግዴለሽ ቢሆን ወይም ጊዜ ለማይሰጥ ነገር ቢዘገይ ይህ ሰው ድካም አለበት።

2. የሌሎችን ድካም ማወቅ

አንድ ሰው ስለሌላው ሰው ድካም ምንድን ነው ማድረግ ያለበት ? ወጣቶች ከመጋባታቸው በፊት የሚያገቡትን ሰው ድካም መፈለግ አለባቸው። ይህም ቃል ኪዳን ከመግባታቸው በፊት መሆን ያለበት ጉዳይ ነው። ከዚያ በኋላ የሚሆን አይደለም። ከጋብቻ በኋላ የሰውን ድካም መፈለግ ስህተት ነው። ከስሕተትም በላይ። ሞኝነት ነው። ከጋብቻ በኋላ እንደዚያ ማድረግ የመሸበት ነገር ይሆናል። ከጋብቻ በኋላ ባልና ሚስት በተቻላቸው እንደ እውርና እንደ ደንቆሮ መሆን አለባቸው። ሳትፈልገው ብዙ ድካም ታያለህ። ታዲያ ብትፈልግማ ምን ያህል ታገኝ ይሆን? ስለዚህ ጋብቻ የሌላውን ሰው ድካም መፈለጊያ አድርገን ልንጠቀምበት አይገባም። ካገባህ በኋላ ዓይኖችህን አትጠቀምባቸው። ነገር ግን ከማግባትህ በፊት ገና እጮኛህን በምትመርጥበት ጊዜ በተፈጥሮ ውበት ታውረህ የሌላውን ሰው ድካም ከመፈለግ አትሰናከል። ለጋብቻ አትጓጓ፣ ከጓጓህ ግን ልታገባ ባሰብከው ሰው ላይ ያለውን ድካም ማየት አትችልም።

3. ሊሸከሙት የሚቻል ወይንም ሊሸከሙት የማይቻል

ድካሞች ሊሸከሟቸው የሚቻሉና የማይቻሉ ናቸው። ድካሞቹ ሊሸከሙአቸው የማይቻሉ ከሆኑ ጋብቻው ሊታሰብ አይገባም። ነገር ግን ድካሞቹን መሸከም የሚቻል ከሆነ ልታገባ ትችላለህ።ይሁን እንጂ

ከጋብቻው በፊት ሁሉንም ድካሞች ልታውቃቸው ይገባል። ከጋብቻ በኋላ ድካም መፈለግ ጥቅሙ ምንድን ነው? ከጋብቻ በኋላ የሚደረግ የድካም ፍለጋ የቤተሰብህን ሕይወት ያቀጭጨዋል። ምክንያቱም ለመለወጥ አስቸጋሪ ይሆናልና ነው።

4. ድካም አይካካስም

አንድ ማስጠንቀቂያ ላስቀምጥላችሁ እወዳለሁ። አንድ ዓይነት ድካም ያለባቸው ሰዎች ባንድነት ይኖራሉ ብላችሁ እንዳታስቡ። ብዙዎች የተሣሣተ መረዳት አላቸው። እነዚህም ሰዎች ተመሣሣይ ድካም ካለው ሰው ጋር አብረን መኖር እንችላለን፣ የተለየ ድካም ካለበት ሰው ጋር ግን አብረን መኖር አንችልም ብለው ያስባሉ። እንደዚያ የሚባል ነገር የለም። እንዲያውም ለሰዎች የበለጠ ከባዱ ተመሣሣይ ድካም ካላቸው ሰዎች ጋር መኖር ነው። የባህርይ ጉዳይ ቢሆን ችግር የለውም። ነገር ግን ድካም ከሆነ ሁለቱም ያለ ጥርጥር ይሰቃያሉ። ለራሣቸውም ለሌላውም ይሰቃያሉ። ስለሆነም የእነርሱ ችግርና ኃላፊነታቸው እጥፍ ይሆናል። ባሕርይን መሸከም ይቻላል ነገር ግን ድካምን መሸከም አይቻልም፣ ይከብዳል።

ይህ መታወቅ አለበት። ለድካም ይቅርታ ሊደረግለት ይችላል። ነገር ግን ሲሸከሙት የማይቻል ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሁለት ሰዎች ድካም አንድ ዓይነት ባይሆን ይመረጣል።

ሥነ ምግባር

ጋብቻ ስኬታማ እንዲሆን ሁለቱም በጋራ መከባበር ያስፈልጋቸዋል። አንዱ ሌላውን የሚንቅ ከሆነ ግን ቤተሠቡ ይከሰማል። ባል የሚሰቱን ፀባይ ማክበር አለበት። ሚስትም የባሏን ጥሩ ፀባይ ማድነቅ አለበት። ይህ የባህርይ ወይም የድካም ጉዳይ ሳይሆን የሥነ ምግባር ጉዳይ ነው።

ለምሳሌ አልፎ አልፎ ሚስት ውሸት ብትናገር ይቅር ይባላል። ነገር ግን ታማኝ ባትሆንና ሁል ጊዜ ብትዋሽ ይህ ከፋ ሥነ ምግባር ነው። ሌላ ምሣሌ እንመልከት፣ ባል ራስ ወዳድና ስለ ራሱ ብቻ የሚያስብ ከሆነ እንዴት የሚስቱን አከብሮት ሊያገኝ ይችላል ? ባል በቤተሰቡ ውስጥ ቢያንስ ጥቂት የሚደነቁ ጥሩ ጎኖች ሊኖሩት ይገባል። ሥነምግባር ከባህርይ ይለያል። አንድ የሚከበር ወይም የሚደነቅ ነገር ከሌለ ቤተሰቡ ያበቃለታል። የባህርይ ልዩነት ነገሮችን እያከረረ ያመጣቸዋል። ነገር ግን የሚደነቅ ሥነምግባር ከጠፋ የቤቱን መሠረት ድምጥማጡን ያጠፋዋል።

ማነው የትዳር ጓደኛው ሳያደንቀው የቤተሰቡን ደህንነት ሊጠብቅ የሚችል?

አንዳንድ ሰዎች ጨካኝ ናቸው። ሰዎችን ያንገላታሉ፣ የጭካኔ ተግባር ይፈፅማሉ። ሌላው ስለሚሰማው ነገር ሳይሆን ግድ የሚላቸው ስለራሣቸው ስሜት ብቻ ነው። እንግዲህ ይህ የባህርይ ልዩነት ሳይሆን የሥነምግባር ጉድለት ነው። መከባበርን የማያመጣ ምግባር የጋብቻን መውደቅ ያፋጥናል።

አንዳንድ ሰዎች ራሣቸውን መቆጣጠር አይችሉም። በአኗኗራቸው ልቅ ናቸው። ቁጣቸውን ያለገደብ ይገልጡታል። እንዲህ የሚሆኑት ለምንድን ነው? ምክንያቱም ራስ ወዳድ ስለሆኑና የራሣቸውን ርካታ ስለሚፈልጉ ነው። ለአንዳንድ ሰዎች ቁጣ ሲገለጥ በጣም ያረካቸዋል፣ ለሁለተኛው ሰው ግን የዚህ አይነቱ አጠያያቂ ሥነምግባር መዋረድን ያመጣል።

የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ለማንኛውም ነገር ለሚፈልጉ ሰዎች ይህ የተለየ ድርጊት ድካም ሳይሆን የሥነ ምግባር ጉድለት ነው። አንዱ ሰው እጮኛ ሲመርጥ የዚያን ሰው በስነምግባር ሁኔታ መቋቋም እችላለሁ ወይ ብሎ ማሠብ አለበት። ስለዚህ የጋራ መከባበር መኖሩን መፈለግ ያለበት ከጋብቻ በፊት ነው። በተለይ በእግዚአብሔር ልጆች ጋብቻ ውስጥ የሚደነቅ ሥነ ምግባር ያስፈልጋል። የሚደነቅ ሥነ ምግባር የሌለው ሰው ለጋብቻ ብቁ አይደለም። በእግዚአብሔር ፊት ተስማሚ መሆን ያስፈልጋል።

<u>ተስማምቶ አብሮ መኖር</u>

በአንድ ሰው ማንነት ውስጥ ሌላው ሊጠና የሚገባው ነገር ይህ ለጋብቻ የተሰጠው ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር አብሮ መኖር ይችላል ወይ የሚለው ነው። ጋብቻ አብሮ መኖር ነው። አንዳንድ ሰዎች ፍፁም የተለዩ ናቸው ከሌሎች ሰዎች ጋር በሰላም አብረው መኖር አይችሉም። አንድ ሰው ከወላጆቹ፣ ከወንድሞቹና ከእህቶቹ ጋር አብሮ መኖር ካልቻለ ታዲያ እንዴት አንተ ከእርሱ ጋር አስደሰች የጋብቻ ሕይወት እኖራለሁ ብለህ ትጠብቃለህ? አንዲት ሴት ሁል ጊዜ ፀበኛ ከሆነች እርሷን በማግባት የተሳካ የቤተሰብ ሕይወት የመኖሩ ተስፋ አጠያያቂ ነው።

የጋብቻ መሠረታዊ ነገር ከሰዎች ጋር ተስማምቶ መኖር ነው። አንድ ሰው ከሌሎች ጋር መኖር ካልቻለ ያ ሰው ካንተ ጋር መኖር አይችልም። እንደዚህ ዓይነቱ ማንንም የሚዘልፍ ሰው እኔን ብቻ

ያከብረኛል ብለህ ታስባለህ? ከጋብቻ በኋላ አንተንም ይህ ዘለፋ ይደርስሃል።

ለምሳሌ አንዲት ለጋብቻ የደረሰች እህት ለሰዎች ሁሉ እንዴት አባቷ፣ እናቷ፣ ወንድሞቿና እህቶቿ ያስታዩአት እንደነበር የምትናገር ከሆነ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንተንም እንደዚያው እንደምትልህ እወቅ። ይህች እህት ከሌሎች ጋር አብሮ የመኖር ኃይል ይጎድላታል።

አንድ ሰው ከሰው ጋር ተግባብቶ የሚኖር ከሆነ ከአንተም ጋር ለመኖር ቀላል ነው። ይህ ጉዳይ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው።

መቀደስ

እርኅኑነትን በተመለከተ በመጀመሪያ የዳሰስነው ነገር አካላዊ ውበት ማለትም ውጫዊ ገፅታን ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የተመለከትነው የሰውየውን ባሕርይ ማለትም የነፍሱን ገፅታ ነው። አሁን ደግሞ በዚህ በሶስተኛ ክፍል መንፈሳዊ ገፅታውን እንመለከታለን።

1. አንድ ዓይነት ዓላማ

ክርስቲያን የማያምን ሰው ማግባት የለበትም። ወደ ጋብቻ ትልቅ ትርጉም መድረሳችንን ማየት አለብን። ከተፈጥሮ ውበትና ከባሕርይ ወይም ከሥነምግባር በተጨማሪ የመንፈሳዊ ዓላማ አንድነት ሊኖር ይገባል። ይህም ማለት ሁለቱም እግዚአብሔርን የማገልገል ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል። ሁለቱም ሙሉ በሙሉ ለጌታ የተሠጡ ሊሆኑ ይገባል ሁለቱም ለጌታ ሊኖሩ ይገባል።ከሚደነቅ ምግባር ይልቅ ይህ የበለጠ ዋጋ አለው። የሚደነቅ ምግባር ሊታለፍ የማይቻል ቢሆንም ለጌታ መኖር ግን እጅግ አስፈላጊ ነው። በከፍታም ይሁን በዝቅታ ሁለቱም ለጌታ መኖር አለባቸው።

እንደዚህ ዓይነቱ ጋብቻ ፅኑ መሠረት ይኖረዋል። ምክንያቱም ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ጠንካራ አንድነት አላቸውና ነው።

2. የክርስቶስ ጌትነት

አንድ ዓይነት ዓላማ ባለው ቤተሰብ ውስጥ ማን ራስ እንደሚሆንና ማን ማዘዝ እንዳለበት አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም። ሊታዘዙት የሚገባ ክርስቶስ እርሱ የዚያ ቤት ራስ ነው። ፊት የመቋጠር ጥያቄ ያከትማል። ብዙ ባልና ሚስቶች የሚጣሉት "ትክክል ነው ወይም ስሕተት ነው" በሚል ጉዳይ ሳይሆን ፊታቸውን ማዞር በመፈለጋቸው

ነው። ለተቀደሱ ክርስቲያኖች ግን ይህ ችግር አይሆንም። ሁለቱም በጌታ ፊት ፊታቸውን ለመፍታት ፈቃደኞች ናቸው። ሁለቱም ጥፋታቸውን ለመናዘዝ ይችላሉ። ሁለቱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ፍላጎቱ እስካላቸው ድረስ ማንኛውም ነገር በዚያው መሠረት ላይ እልባት ማግኘት ይችላል።

ወንድሞችና እህቶች ፍፁም መቀደስ እንዳለባቸው ሊያውቁ ይገባል። ሁለቱም ወገኖች የታሰበው ጋብቻ ጌታን ለማገልገል እንደሆነ በልባቸው ካሰቡ የጋብቻቸው መሣካት እጅግ ከፍተኛ ነው። ሌላው ቀርቶ የባህርይ ልዩነቶችና የተፈጥሮ ውበት መደብዘዝ ቢኖር እንኳ ያለ ምንም መሠናክል ቤተሰቡ ይበለፅጋል። ወጣት ወንድሞችና እህቶች ለጋብቻ እነዚህ ሁኔታዎች እንዳሉ እንዲያዩ እግዚአብሔር ያስችላቸዋል። በቀላል አነጋገር እነዚህ ነገሮች በሶስት ይከፈላሉ። እነዚህም ውጫዊ÷ስነልቦናዊ እና መንፈሳዊ ናቸው። እነዚህ ሶስት ነገሮች በትክክለኛ ቅደም ተከተላቸው ሊቀመጡ ይገባል።

አንድ የበለጠ ዋጋ ሊሠጠው የሚገባ ነገር አለ። የሁለተኛው ትውልድ ቤተሰብ ለሁለተኛዋ ትውልድ ቤተ ክርስቲያን የበለጠ መሥራት አለበት። ለሚቀጥለው ትውልድ ቤተሰብ መልካም እንክብካቤ ካደረግን ለሚቀጥለው ትውልድ ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ጥንቃቄ እያደረግን ነው። የተተኪው ትውልድ ቤተሰብ በችግር ተሞልቶ ከመጣ ግን የእኛ አገልግሎት የቤተሰብ ችግርን በመፍታት ጊዜአችንን ማባከን ይሆናል። አስቀድመው ያገቡ ሰዎችን ሁኔታ መለወጥ አንችልም። ልናደርግ የምንችለው እነርሱን ተከታትለን እንዲስተካከሉ፣ እንዲዋደዱና ፍቅር እንዲኖራቸው መርዳት ነው። ነገር ግን ገና ላላገቡት እኛ የምንጠብቀው ጥሩ የቤተሰብ ሕይወት እንዲኖራቸው ነው።

እንግሊዝ አገር በነበርኩበት ጊዜ ጌታን የሚያገለግሉና በእግዚአብሔር መንገድ በአንድ ላይ የሚመላለሱ ብዙ ባልና ሚስቶች አጋጥመውኛል። እንደዚህ ዓይነቱን ሁኔታ ማየት በጣም ግሩም ነው።

ባልና ሚስት እግዚአብሔርን በአንድ ልብ ሲከተሉ ማየት ውብና አስደሳች እይታ ነው። ስለዚህ በእድሜ የሸመገሉ ወንድሞችና እህቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ወጣቶችን ቢረዱአቸው እነዚህ ወጣቶች ከብዙ ስህተት ይድናሉ። እግዚአብሔር ሁሉንም እህቶችና ወንድሞች ይባርክ። አሜን።